# የእግዚአብሔር መንግሥት

*"… መንግሥቱ ሁሉን ትገዛለች"*

*መዝ. 103፥19*

በመጋቢ አብርሃም ኢሳይያስ

2004/2012

**የመጀመሪያ እትም 2004**

First Edition 2012

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱሶች ከመጀመሪያ እትም የአማርኛ መደበኛ ትርጉምና ከሙሉእ ሕይወት የተወሰዱ ናቸው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት በቅድሚያ የጸሓፊው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

**አሳታሚና አከፋፋይ**
**ሰሜን ገበያ አዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን**
✉ 25549
አዲስ አበባ

E-mail Sgakbc@yahoo.com
☎ 011-1-55 42 98



# ስጦታ

ለ ____________________

ከ ____________________
ፊርማ ____________________
ቀን ____________________

# አበርክቶት

መስጠትን እንድያ ልጁን ሳይሰስት ከሰጠን አምላክ ተምረናል (ዮሐ. 3፥16)።

የመጀመሪያ የሆነውን የበኩር ሥራዬን "ክርስቶስን ወደ መምሰል ማደግ" የሚለውን መጽሐፌን ሊመርቅ ሦስት ቀን ሲቀረው "ወደ ቤቴ ስትገባው" የሚለውን ድምጽ ስሰማ ሳላመነታ ሰጠሁት፣ በሚገርም ፍጥነት ሦስት ወር ሳይሞላ በገበያ ላይ አልቆ ሁለተኛው እትም ታተመ፤ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሁሉ መታነጽ አድርጎት አየሁት። ይኽንንም ሁለተኛ መጽሐፌን እንዴ ለእርሱ በመስጠት የሚገኘውን በረከት ተለማምጀዋለውና ለእርሱ ሥራ በተለይ ቤተ ክርስቲያናችን ለቦታ ግዢ ለምታደርገው የገንዘብ ማሰባሰብ ገቢ እንዲሆን አበረክቻለሁ።

ሰሜን ገበያ አዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን በቀጨኔ ውስጥ የመንግሥቱን ሥራ በመሥራት ላይ የምትገኝ ስትሆን፣ ከሕዳር 2004 ዓ.ም ጀምሮ ቦታ ለመግዛት በተለያየ መንገድ ገንዘብ በማሰባሰብ ላይ ትገኛለች።

ይኽን ቅዱስ ሥራ በገንዘባችሁ ለመደገፍ የምትፈልጉ የባንክ ቁጥራችን በኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን ሰሜን ገበያ አጥቢያ አራዳ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 3024/01718850061500 በሚል ማስገባት ይቻላል።



# ምስጋና

## "ሁሉም በእርሱ፣ በእርሱ ነውና፣ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን"

(ሮሜ 11፥39)

አነሳስቶ ላስጀመረኝ፣ አስጀምሮም፣ ላስጨረሰኝ አምላክ ሰብሃት ይሁን።

ይህችን መጽሐፍ ስጽፍ በሃሳብና በጸሎት የረዱኝን ቅዱሳን ሁሉ በጌታ ስም አመሰግናለሁ። ነገር ግን በዚህ ሥራ ውስጥ በተለየና በተገለጠ መንገድ ከጎኔ የቆሙትን ወንድሞቼና እህቶቼን ገጹ የሚፈቅድልኝ ያህል በስም በመግለጽ በአንባቢያን ፊት ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በቅድሚያ የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ የጻፈችውን ዓለም ፈቃድን (ቤርያ) እንዲሁም ከሥር ከሥር የጹሑፉን ሥራ በማረም የረዷትን ኤልያስ ጌትነትና ታሪኩ ሰለሞን እናንተን ሳላመሰግን አላልፍም። ደግሞም የፊደል ግድፈትና የሥርዓተ ነጥብ መዛባት እንዳይኖር የተቻላቸውን ጥረት ያደረጉትን ወ/ም መዝገቡ አሰፋና ወ/ም ሽምሰዲን እንዲሁም የሽፋን ሥዕሉ በመስራት የተለመደ ትብብሯን ያሳየችኝን እህት ሰናይት ደጀኔ ለቀና ትብብራችሁ ምሥጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

መጽሐፉን በማንበብ አስተያየት በመስጠት እንዲህ ብትለው ወይም ብታደርገው ጥሩ ነው፤ በማለት ምክርን የለገሳችሁኝን ዶ/ር ሳምሶን እስጢፋኖስና ፓ/ር ንጉሴ ሃይሌን በእውነት በማገለግለው ጌታ ስም ልባዊ አክብሮቴን እገልጻለሁ።

እኔ የብዙ ሰዎች ውጤት ነኝ። ይኸም ክርስቶስን በመምሰል እንዳድግ መንፈስ ቅዱስ መሳርያ አድርጎ የተጠቀመባቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። ከመጀመሪያው ከመሠረት መጣያ ትምህርት አንስቶ፣ እስከ አሁን ድረስ ማለት ነው። ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ሰዎች መጥራት ጊዜውም ወረቀቱም አይበቃል። ቢሆንም አምላኬ ያውቃቸዋልና ለበረከት ሁኑ!

እንግዲህ ይህቺን መጽሐፍ ለምታነቡት ሁሉ መልካም ንባብ ይሆንላችሁ ዘንድ በመመኘት እዚህ ላይ ላብቃ፤ እናንተ ግን ንባቡን ቀጥሉ . . . . .



## ማውጫ

መግቢያ ............................................................................

1. የእግዚአብሔር መንግሥት ትርጓሜና ምንነት ............2

2. የመንግሥቱ ሕገ መንግሥት ............................27

3. የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ............................38

4. በመንግሥቱ ውስጥ የሚሰራ መንፈስ ..................48

5. በመንግሥቱ መኖር ............................................61

6. የመንግሥቱን ራዕይ መያዝ ..................................68

7. የመንግሥቱ ዜጋ ................................................86

8. መንግሥቱን ማስፋት ........................................101

9. የመንግሥቱ በሙላት መገለጥ ..........................114

ማጠቃለያ ..........................................................125

## መቅድም

"የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና" (ሮሜ.14÷17)፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሰዎች ልብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይመሰርት ዘንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ሰባኪ ሆኖ መጣ እንጂ በአገልግሎቱ "የፈውስ ሰባኪ" ወይም "የእምነት ሰባኪ" አልነበረም፡፡ ይልቁኑ "...የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል..." (ሉቃ.16÷16) እንደሚለው ቃል በሰዎች መካከልና ልብ ውስጥ የሚመሠርታትን መንግሥቱን አስተዋወቃአቸው፡፡ ምድርንም በሰማይ ቅኝ አገዛዝ ሥር ትገባ ወይም ትሆን ዘንድም መምጣቱን መንግሥቱን ሲመሰርት አውጇል፡፡ ይህም የቅኝ ግዛት ዓላማው መንፈሳዊ የሆኑ የመንግሥቱ ልጆች ሰማያዊ የሆነ እሴት፣ ባህል፣ በአኗኗራቸው በመግለጥ የመጡበትን (የተገኙበትን) መንግሥት በማሳየትና በጨለማው አገዛዝ ውስጥ ላለችው ዓለም ዜጋ የሆኑባትን አገር የምትመስል መንግሥት ማስፋፋት ጥሪያቸው መሆኑን በትምህርቱ ገልጦላቸዋል፡፡

እግዚአብሔርም አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ሰማያዊው መንግሥት ምን እንደሚመስል ፍንጭ ሰጥቶናል፡፡ ይህም በነቢዩ ዳንኤል አማካኝነት ከዓለም መፈጠር በፊት የነበረውን ሃሳቡንና በዓለም ፍጻሜ የሚሆነውን በመንገር የመንግሥቱን ገዢነት በመንፈስ አሳይቶታል (ዳን. 2÷44)፡፡ የመንግሥቱ አመሰራረት የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራ ነው (ዳን. 2÷45) "ከተራራ ተፈንቅሎ" የሚለው የሚያሳየው ተራ ከሆነው ግዙፍ ነገር መለየትና መውጣት የሚያመለክት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከሰው መንግሥት



ትለያለች፣ የሰውንም የጨለማውንም መንግሥት በመጨረሻም ትገዛለች ፣ ታደቃለችም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም የሰማይ መንግሥት በሚል ቃል ተገልጦ የምናገኘው ሃሳብ ያው አንዱን መንግሥት ለመግለጥ መሆኑን መረዳት አለብን፡፡ በተመሳሳይም ማቴዎስ በጻፈው ወንጌል ውስጥ ደግሞ መንግሥቱን "መንግሥተ ሰማይ" በማለት ገልጾታል፡፡

በመንግሥት ሰማይና በእግዚአብሔር መንግሥት መካከል መሠረታዊ የሆነ የትርጉም ልዩነት የለውም፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ መረዳት ማቴዎስ ንጉሱ የሚገዛበትን ሥፍራ ለማመልከት "መንግሥተ ሰማይ" ሲል፤ ማርቆስ ደግሞ የንጉሱን አገዛዝ ለማሳየት "የእግዚአብሔር መንግሥት" በማለት ይገልጸዋል፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት አንዱ ትርጉም ፈቃዱ የሚፈጸምበት ክልል (ስፍራ) ይሆናል (ማቴ. 6÷9-10)፡፡ የሰማይ ንጉስን ፈቃድ ለመፈጸም "በሰማይ እንደ ሆነች በምድር ትሁን" እንደሚለው ለማድረግ በሰማይና በተገዢው መካከል ግንኙነት ሊኖር ግድ ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችለው በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ አማካኝነት ዳግመኛ በመወለድ ነው፡፡ ያኔ ነው እንግዲህ ሰዎች የጌታን ፈቃድ በጸጋው ብርታትና በእምነት ለመተግበር መቻላቸው የሚረጋገጠው፡፡

በእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ መንግሥቱ በሰው ልብ ተዘርቶና አድጎ በመንፈሳዊ ገፅታ ብቻ ሳይሆን በአካላዊ ሁኔታ ሲገዛ ማየት የማይወድቅ አሳቡ ነው፡፡ ከዓለም መፈጠር በፊት የሚታየው ነገር ሁሉ ከማይታየው ዓለም ከመምጣቱ በፊት ለሰው ሊሰጠው (ሰውን ሲፈጥር) ያሰበው ምን ይሆን? ብለን ከጠየቅን መንግሥት ለመስጠትና ለማወርስ መሆኑን ቃሉ በማያሻማ መልኩ ይገልጸዋል (ማቴ. 25÷34)፡፡ ሰዎችም መንግሥቱን ይፈልጓት ዘንድ

ጌታ ኢየሱስም አስተምሯል እንዲህ በማለት “ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥቱን እሹ (ፈልጉ) ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል” (ማቴ. 6፥33)።

*የእግዚአብሔር መንግሥት፣ የጽድቅ መንግሥት፣ የሰላምና የፍቅር መንግሥት፣ መንፈሳዊም መንግሥት ናት* (ዕብ.12፥14፣ ዘጸ. 28፥36፣ ኢሳ. 9፥6፣ 2፥4፣ ሉቃ. 2፥4፣ 1ቆሮ. 15፥20)።

*የእግዚአብሔር መንግሥት ሕገ-መንግሥት የንጉሡ ሕይወት* (ወግ፣ ደንብ፣ ሥርዓት) ነው (ኢሳ.11፥1-10፣ ማቴ. 5፥7)። *ይሄ መንግሥት መንፈሳዊ ባሕሪያትና ሰማያዊ* ጥበብ የሚገለጹበት ነው። በአጭሩ የእግዚአብሔርን *መንግሥት ልንረዳውና ልንለየው እንችላለን። የጽድቅ ኑሮ የሚደበቅ አይደለምና። ነገር ግን መንፈሳዊ እውነት ስለሆነ መንግሥቱን ለመረዳት መንፈሳዊ አእምሮ (መረዳት) ያስፈልጋል።*

*መጥምቁ ዮሐንስ ቀርባለች ያላት የሰማይ መንግሥት* (ማቴ. 3፥2) *ጌታ ኢየሱስ እንዲሁ ያስተጋባት* (ማቴ.4፥17) *መንግሥት የምትገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ልከኛ የሆነች* ልብ ውስጥ ነው (ሉቃ.17፥20-21)።

የክርስቶስ ኢየሱስ *ጸጋ* ልብን (አእምሮን) እስካለወጠ ድረስ የእግዚአብሔር *መንግሥት* እውነታ ከሰዎች እንደ ተደበቀች ትቀራለች። አዲስ ኪዳን በግልጽና በብዙ ማስረጃ የእግዚአብሔር *መንግሥት* ከሕዝባዊ *ሥልጣን* ጋር እንደማይወዳደር ወይም እንደማይመሳሰል ያስረዳል። ሁለቱም *መንግሥታት* የተለያዩ ናቸው። አንዱ *መንፈሳዊ* ሌላኛው ደግሞ ዓለማዊ ነው።

እንግዲህ *መንግሥት* በንጉሡ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣና በአሁኑ ጊዜ በመንፈሳዊ መልክ በቤተክርስቲያን የተገለፀ፣



ወደፊት ደግሞ በሙላት በሚታይ መልኩ አገዛዙ በአካላዊ መንገድ በምድር ላይ በገሃድ የሚገለጽ ነው።

# ጥቂት ለግንዛቤ

መንግስት የሚለውን የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንዲህ ይገልጸዋል፣ የአንድ አገር ህዝብና የግዝአት ስርዓት በማለት፡፡ ስለዚህ መንግሥት የሚለው ቃል ህዝቦችንና ሕጉ ወይም የሚተዳደሩበት ሥርዓትን ይመለከታል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ደግሞ መንግሥት የሚለው ቃል ቢያንስ ሦስት ትርጓሜ ይዛል፡-

I. መንግሥት ሕዝብን ለማመልከት፣

"ለወደደን ከኀጢአታችን በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገን ..." ራዕ. 1፥6 (ዘጸ.19፥5-6፣ 1ጴጥ. 2፥9-10)፡፡

II. መንግሥት ጌታ ኢየሱስን ለማመልከት፣

". . . እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው" (ሉቃ. 17፥21)፡፡

III. የእግዚአብሔር አገዛዝን ለማመልከት፣

"መንግሥቱ ሁሉን ትገዛለች" (መዝ. 103፥19፣ ሮሜ 14፥17)፡፡

ስለዚህ ስለ መንግሥቱ የተሰጠው አንድ ወጥ ትርጉም አይደለም፡፡ ይልቁኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተጠቀሰበ አውድ ትርጉሙ ይወሰናል፡፡



የተጨማሪም ይህንን ሥዕላዊ መግለጫ እንይ፡-




በሰው መንግሥት ውስጥ የሚንጸባረቀው የመንፈሳዊ መንግሥት አሻራ ሲሆን፣ እነዚህ ሁለት መንግሥታት የሰውን መንግሥት ለመያዝ ፍላጎትንም ያሳያሉ፡፡ ዳንኤል በሚጸልይበት ጊዜ ጸሎቱ በጊዜው እንዳይመለስ የሚቃወመው በሚታየው መንግሥት የተሰየመው የፋርስ መንግሥት አለቃ ነበር ዳን.10.13፡፡ ጦርነቱም በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እንደተከናወነ ክፍሉን ግልጽ ያደርግልናል ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

"... የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠበቅ አትመጣም፤ ደግሞም፦ እንኋት በዚህ ወይም፦ እንኋት በዚያ አይሉአትም፡፡ እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው፡፡

ሉ.ቃ. 17፥20-21

# 1

## የእግዚአብሔር መንግሥት ትርጓሜና ምንነት

የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስልሳ ዘጠኝ ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ተመሳሳዩ ቃል የሰማይ መንግሥት የሚለው ደግሞ ሰላሳ ሁለት ጊዜ ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ ይህ መረጃና ትምህርት መሰረቱ በልብ ላይ ከሆነው ቃል ኪዳን ጋር ነው (ኤር. 31፥31) ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ትርጓሜ ከማየታችን በፊት በቅድሚያ መንግሥት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት፡- መንግሥት የራሱ ግዛትና ድንበር ያለው፣ በሚገዛበት ክልል የሚመራቸውና የሚያስተዳድራቸው ሕዝብ ያሉት፣ የሕዝቡንም መብትና ግዴታ የሚወስንበት ሕግ ያለውና በግዛቱ ላይ ነፃ የሆነ ምሉእ ስልጣን ያለው አካል ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትስ? የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር በሙሉ ስልጣኑ፣ በኃይሉ፣ በክብሩ የሚገዛውና የሚያስተዳድረው መንፈሳዊ መንግሥት ነው፡፡ "...የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሳል ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፡፡ እነዚህንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፤ ታጠፋቸዋለች፤ ለዘላለምም ትቆማለች፡፡" ዳን. 2፥44፡፡ ይህም እግዚአብሔር ንጉስ ሆኖ በማይታየው ዓለም

የሚኖሩትን መንፈሳዊ ፍጥረታትን (ቈላ.1፥16) እንዲሁም በሚታየው ዓለም በሰው አስተዳደር ላይ የሰለጠነ “. . . ልዑል በሰዎች መንግሥት ሁሉ ላይ እንደሚገዛና. . .” (ዳን. 4፥17) እንደሚል፤ በሁሉ መንግሥታት ላይ ገዢ የሆነበት፤ ደግሞም በክርስቶስ በአደረገው ሥራ ወደ እራሱ አገዛዝ ያፈለሳቸው ሕዝብ (ዜጎች) ያሉት “. . .እርሱ ከጨለማ ግዛት ታደገን ወደ ሚወደው ልጁ መንግሥት አሻገርን” ቈላ. 1፥13። እንዲሁም ዜጎቹም የሚተዳደሩበት ደንብና ሕግ ያላቸው ሲሆኑ፤ ዜጎቹም የመንግሥቱ መተዳደሪያና ወግ የሆነውን የመንግሥት ቃል የሚሰሙና የሚታዘዙ ናቸው (ማቴ.13፥19)።

የእግዚአብሔር መንግሥት በብሉይ ኪዳን በትንቢታዊ መልኩ ወደ ፊት እንደምትመጣና እንደምትገለጥ በመናገር ነቢያቶች አስቀድመው በመረዳት ይህን የእግዚአብሔር ሐሳብ አገልግለዋል። በአዲስ ኪዳን ግን መንግሥቱ ወደ ሰዎች ግዛት (መንግሥት) በንጉሱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣችና የምትመጣም ናት። ይኸም ማለት በአሁኑ ዘመን ያለችና ወደ ፊት በሙላት በመምጣት የምትገለጥ ናት “... መንግሥትህ ትምጣ...” (ማቴ. 6፥10)።





## የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ መጣች?

የእግዚአብሔር መንግሥት ጅማሬን ያገኘችዉ በሰማይ (በመንግሥተ ሰማይ) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የዘላለም ንጉስ እንሆነ ያስተምራል። ጥያቄው ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ጅማሬ በምድር “መቼ?” የሚል ነው። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት በፊት መንገድ ጠራጊው ሆኖ የተላከው ነቢዩ መጥምቁ ዮሐንስ ስብከቱን የጀመረው ስለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲህ ብሎ በመናገር ነበር “...በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት (የእግዚአብሔር መንግሥት) ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ” (ማቴ. 3፥1-2) ይላል። ጌታ ኢየሱስም ሲናገር “ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ሲነገሩ ኖረዋል፤ ከዚያ በኋላ ግን የእግዚአብሔር መንግሥት የምስራች ተሰብኳል፤ሰውም ሁሉ ወደዚያ ለመግባት ይጋፋል” (ሉቃ.16፥16) በማለት። መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ሲሆን፤ አገልግሎቱም ከአሮጌው ወደ አዲሱ ኪዳን የሚያሸጋግርና መንግሥቱ እንደቀረበ የሚያመለክት ድምጽ ሆኖ ነበር ያገለገለው (ኤር. 31፥31፤ ዕብ. 8፥6-12)። የጌታ ኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ግን የአዲስ ኪዳን ዘመን ያመጣና ፣አሮጌውን የኪዳን ዘመን ወደ ፍጻሜ ያደረሰ፤ መንግስቱም እንደ መጣች ያበሰረ ነበር።

ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዙሪያው ለተሰበሰቡት ሕዝብ መንግሥቱ በመካከላቸው እንደሆነ የገለጸው (ሉቃ.17፥20-21)።

ንጉሱ ባለበት መንግሥቱ አለ፤ ስለዚህ መንግሥቱ የመጣችው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ሲሆን በኃይል የተገለጠችው ግን በቤተ ክርስቲያን ውልደትና በመንፈስ ቅዱስ መምጣት ነው። ለደቀ መዛሙርቱ የተነገራቸው እንዲህ ነው "እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳያዩ ሞትን የማይቀምሱ ሰዎች አሉ" (ሉቃ. 9÷27) በማለት። ይህ ክፍል በመጨረሻ ዘመን በሙላት ስለሚገለጠው መንግሥት የሚናገር ሳይሆን፤ ይልቁኑ በጰንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሲወረድ መንግሥቱን እንደሚያዩ የሚያሳይ ነው (የሐዋ. 2÷1-47)። ሐዋሪያትም በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ እንዲሁም በመሞላት መንግሥቱን በድንቅና በተአምራት እየሰበኩና እያስተዋወቁ ወደ ዓለም ሁሉ ይዞሩ ነበር "አሁንም ቢሆን፣ በመካከላችሁ ተዘዋውሬ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበክሁላችሁ፣.." (የሐዋ. 20÷25) ይላል። የሰብከታቸዉ ርዕስ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ እንደ ነበር ያሳያል።

የእግዚአብሔር መንግሥት በየት ነው? የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ





እንደምትመጣ የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት ነበራቸው። ለዚህም ምክንያት የሆናቸው በጊዜው በሮማውያን ቅኝ አገዛዝ በመኖራቸውና የሮማ መንግሥት የእሥራኤልን መንግሥት አፈራርሶ ስለነበረ ነው። በርግጥ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ለፈሪሳውያን ብቻ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ጭምር ያሳስባቸው እንደነበር ማየት እንችላለን። "ጌታ ሆይ፤ የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን?" (የሐዋ. 1÷6) ብለው ጠይቀዋል። ለደቀ መዛሙርቱ ያላቸው "ይህንን ማወቅ ለእናንተ አልተሰጠም" በማለት በመንፈስ ቅዱስ መውረድ አማካኝነት በሚቀበሉት ኃይል የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩ ሲያዝ እናያለን። ለሃይማኖት መምህራን ለሆኑት ግን የመለሰላቸው የእግዚአብሔር መንግሥት በዐይን የምትታይ ሳትሆን መንፈሳዊ (ሰማያዊ) መሆኗን በመናገር መንግስቱ በሰዎች ልብ ውስጥ የምትኖር ወይም በእነሱ መካከል የምትሰራ መሆኑን አመለከታቸው።

የእግዚአብሔር መንግሥት ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የመጣች መንፈሳዊ ይዘት ያላት አካል ናት እንጂ፤ በጊዜው የነበሩት የሃይማኖት መሪዎችና ሕዝቡ በሚጠብቋት መንገድ ማለትም እንደ ምድራዊ መንግሥታት በጦርና በወተደራዊ ኃይል የታነጸና ሮማዊያን ድል በማድረግ ከቅኝ አገዛዝ ነጻ የወጣች እስራኤል የምታስገኝ ሳትሆን፣

ይልቁንም ሰዎችን፣ የኀጢአት፣ የደዌ፣ ባሪያ ካደረገው የሰይጣንን ኀይል፤ አርነትን ለመስጠት የተገለጠች መንግሥት ናት ።

የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች መካከልና በሰዎች ልብ ውሥጥ ትኖራለች፤ ይህን ቃል የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለዋል፣ "with in you"/N.k.j.v/ "በእናንተ ውስጥ" በማለት ግዛቱንም በሰው ልብ እንደሚያደርግ ያሳያል። መንፈስ ቅዱስም ጽድቅ፣ ሰላም፣ ደስታ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ውስጥና መካከል በማፍሰስ መንግሥቱን ይገልጣል (ሮሜ 14÷17)።

የጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ጅማሬ ምን ይመስላል? መጥምቁ ዮሐንስ መንግስቱ ቀርባለች በማለት የጀመረው አገልግሎት በይፋ ከመንፈስ በአገኘው መረዳት ለመሲሁ ሲያስረክብ (ዮሐ.1÷26-30)። ጌታም በእርሱ የመጣችውን መንግሥት በማስተዋወቅ፣ የመንግሥቱን ምንነት በመግለጽ ነበር አገልግሎቱን የጀመረው (ማቴ.4÷17)። በስብከቱም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሕዝቡ ሁሉ በሚረዳው መንገድና በምሳሌ ያስተምራቸው ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ይህችን የመጣችውን ደግሞም ወደፊት በሙላት የምትገለጠውን መንግሥት በተለያየ መልኩ ዘግበውታል። በተለይ ደግሞ ማቴዎስ ለፊውን የመጽሐፉን ምዕራፍ





ስለመንግሥተ ሰማይ (የእግዚአብሔርን መንግሥት) ምስጥራት ጽፎ እናገኘዋለን። ለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ሰፋፊ ትምህርቶችን የያዘ መጽሐፍ ነው የሚባለው። ከዚህም አንፃር መፅሐፉ 60 በመቶው በኢየሱስ ትምህርቶች ላይ ያተኮረ ነው ማለት ይቻላል። እነዚህ ትምህርቶች ለአጠቃላይ ግንዛቤ ያህል የሚገኙበት ምዕራፎችና ያስተማራቸው ርዕሶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- 5-7 የተራራው ትምህርት
- 9፥35-10፥42 ለሐዋርያት የተሰጠው ሐላፊነት
- 13 የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች (የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጥራት)
- 18፥1-35 የይቅርታና፣ የትህትና ትምህርቶች
- 24-26 የመጨረሻው ዘመን ትምህርቶች

በዋናነት ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ሶስተኛውን ወይም የመንግሥት ሰማያት ምሳሌ (ምስጥራት) የሚለውን በመመልከት የእግዚአብሔርን መንግሥት ምንነት በቀረብልን ምሳሌ ለመረዳት እንሞክር። ለመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመንግሥተ ሰማይ (ስለ እግዚአብሔር መንግሥት) ምንነት ለማስተማር በምሳሌ ለመጠቀም ለምን ፈለገ? ደግሞስ የምሳሌዎቹስ ዓለማ ምን ነበር? እነዚህን

ጥያቄዎች ብልህ ደቀ መዝሙር ይጠይቃል፤ መንፈስ ከቃሉ የሚያስተምረውንም ይይዛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ያስተምር የነበረው በነቢያት የተነገረው እንዲህ የሚለው ትንቢታዊ ቃል "አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ከጥንት በነበረ እንቆቅልሽ እናገራለሁ፤" (መዝ. 78፥2፣ ማቴ. 13፥35) ይፈጸም ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕግና በነቢያት የተነገረው ቃል ፍፃሜ ሆኖ መጥቷል፤ ስለ እርሱ የተባለው ሁሉ ፍጻሜን አግኝቷል፡፡ ሁለተኛው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምራቸውን ትምህርት ለመረዳት ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ ስለሚቸገሩ በቀላሉና ሊረዱትና ሊገነዘቡት በሚችሉት መጠን በማሰብ ፍጥረታዊን ነገር እንደ ማስረጃ በማቅረብ መንፈሳዊን ነገር የማሳየት ልማድ ስለ ነበረው ነው፡፡ በርግጥ የጌታ ትምህርት ለሕዝቡ ብቻ ሳይሆን፤ ሁሉን ትተው ለተከተሉት ደቀ መዛሙርት እንኳን አንዳንዴ ለመረዳት የሚያስቸግር ነበር፤ ለዚህም ነው ሐዋርያቱ ከጌታ ጋር ለብቻቸው ሲሆን የመጠየቅ ልማድ የነበራቸው፡፡

መንፈሳዊን ነገር ወይም የጠለቀውን የእግዚአብሔርን ልብ ለመረዳት ጊዜን መስጠትና ለመማር የተዘጋጀ ልብ መያዝ ይጠይቃል! እንጂ ብልጭታን በማየት በለብለብ ዕውቀት መሮጥ ከፊል የሆነውን ሐሳብ ማወቅ፤





የሚፈለግብን ደረጃ ላይ አያደርስምና ከወዲሁ መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥቱን ወንጌል ለሕዝብ ሁሉ በከተማ፣ በገጠር፣ በተራራ፣ በወንዝ ዳር፣ በቤተ መቅደስ፣ በየምኩራቡ፣ በገበያና ሕዝብ በተሰበሰበት ሁሉ በመስበክና በማስተማር ይዞር ነበር፡፡ እንግዲህ ከዚህ ድርጊቱ በመነሳት የመንግስቱ ጉዳይ አንገብጋቢ መልዕክት እንደ ነበርና ሰዎች ሁሉ ሊሰሙትና ሊቀበሉት የሚገባ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በይበልጥ የመንግሥቱን ምንነት ልዩ ልዩ በሆነ ምሳሌዎች በመጠቀም ሲያስረዳቸው ስናይ የወንጌል መልዕክት መንግስቱ እንጂ ሌላ አለመሆኑ መገንዘብ እንችላለን፡፡

የማቴዎስ ወንጌል 13ኛውን ምዕራፍ ጊዜ ሰጥተን እንደ መንግሥተ ሰማይ ደቀ መዝሙር እንመልከት፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ሦስቱ ምሳሌዎች መንግሥተ ሰማይ (የእግዚአብሔር መንግሥት)ምን እንደምትመስል ከመንግሥቱ ጅማሬ አንስቶ በሰዎች ልብ ውስጥ ስለሚኖረው ዕድገት በተብራራ መልኩ ተገልጾ እናያለን፡፡ መንግሥተ ሰማይ ምን ትመስላለች?

### 1.1. የዘሪው ምሳሌ ማቴ. 13፥1-9፣ 18-23

ምሳሌው የሚጀምረው አንድ ገበሬ ዘርን ሊዘራ ወጣ በሚል ነው፡፡ ይኸም የሚያሳየን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዴት በሰው ልብ ውስጥ እንደ ዘር በመዘራት እንደሚጀምር የሚያሳይ ነው፡፡ ቃሉን የመስበክና የማስተማር አገልግሎት የከበረ የሆነበት ምስጥር ወደ ሰው ልብ መንግሥቱን ማምጣት በመቻሉ ነው፡፡ ዘሩ የእግዚአብሔር ቃልን ይወክላል፤ የተለያዩ የመሬት ዓይነቶች ደግሞ የተለያዩ የሰውችን ልቦች ያመለክታል፡፡ ደግሞም ልቦች የተለያዩ ዓይነት ምላሽ እንዲሁም ውጤትን ለተዘራው ዘር (ለእግዚአብሔር ቃል) ሲያሳዩ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ አራት መሬቶች(ልቦች) ምን ዓይነት ናቸው?

አንድኛ በመንገድ ዳር የወደቀ ዘር፣ ሁለተኛ አፈሩ ስስ በሆነ ድንጋያማ መሬት ላይ የወደቀ ዘር፣ ሦስተኛ በእሾህ መካከል የወደቀ ዘር፣ አራተኛው በመልካምና በሚያፈራ ለም በሆነ መሬት ላይ የወደቀ ዘር በሚል ምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር እናያለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይኸን ምሳሌ ሲናገር ከደቀ መዛሙርቱ ያገኘው ምላሽ ስለምን በምሳሌ ትናገራለህ የሚል ነበር፡፡ ጌታም ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር ማወቅ





ተሰጥቶአችኋል በማለት ደረጃቸውን ከተራው ሕዝብ ላቅ ያለ መረዳት (የተዘጋጀ ልብ እንዳለቸው) ገለጸላቸው፡፡

ደቀ መዝሙር የሆነ ጌታው የሚያድርገውን ያውቃል፣ ደግሞ ባወቀውም ይመራል፣ ይኖረዋልም እንጂ ተራ (መደዴ) አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን እውነተኛ የጌታ ደቀ መዝሙር ለመሆን የወሰኑ እያልኩ እንጂ፤ የእኛን ቲፎዞ ወይም ጋሻ ጃግሬዎቻችን የሆኑትን “ደቀ መዝሙር” አለመሆኑን መረዳት ብልህነት ነው፡፡ ለመቆጣት አትቸኩሉ! ውድቀታችን በዝቷልና እንዘን! የተሰጠን የእግዚአብሔርን መንጋ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለማድረግ መጠራታችን እንዘንጋ፡፡ስለዚህ በጥንቃቄ እንሒድ፤ የተልዕኮአችንን መሰረትንም እንያዝ ሰዎችን የጌታ ደቀመዝሙር እናድርግ (ማቴ.28.19-20) ፡፡ ያን ጊዜ ጌታ እንዲህ ይላል ለእናንተ እግዚአብሔርን መንግስት ምስጥር ማወቅ ተሰጥቷችኋል፡፡ በእርሱ ለእርሱ ካልሆን ግን መንግሥቱ ምስጥር ይሆንብናል፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመረዳት ልቡን ላዘጋጀ ደቀ መዝሙር የሚበዛ መገለጥ አለው፡፡ ለመረዳት ላልተዘጋጀው ግን ያው ያለው እንኳን እንደሚወሰድብት ጌታ በማስጠንቀቅ ተናግሯል “ላለው ይጨመርለታል ይበዛለትማል

ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል" (ማቴ. 13፥12) ፡፡ የዘሪው ምሳሌ ትርጉም ምን ይሆን፡-

የመጀመሪያው ምሳሌ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር፣ አመልካችነቱ ያልተዘጋጀ ልብ ያለውን ሰው ሲሆን የእግዚአብሔር ቃል ወደ እንደነዚህ ዓይነት ልብ ዘልቆ አይገባም፡፡ የተዘራውንም ዘር ሰይጣን ወዲህና ወዲያ ሲዞር እንደ ወፍ ቃሉን ከልባቸው ይወስዳልና በሕይወታቸው ፍሬ ሊኖራቸው አይችልም፡፡

እነደነዚህ ዓይነት ሰዎች መጀመሪያም የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ለመታዘዝና በቃሉ ለመኖር ልባቸውን አዘጋጅተው ስላልሆነ የመጡት፤ ስለዚህም ጌታ በመጀመሪያም ከእነርሱም ፍሬ አይጠብቅም፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ እነዚህን እንዲህ ይላቸዋል "..ቃሉ ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሃደ አልጠቀማቸውም" (ዕብ.4÷2) ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን በእምነት ሲዋሃድ ብቻ እንጂ የሚጠቅመን፤ ሰሚዎች ብቻ ከሆን አይጠቅመንም፡፡ የበላነው ምግብ እንኳን ሲዋሃደን ብቻ ነው ሰውነት የሚሆነንና የሚጠቅመን ካልተዋሃደ ከወጣ ግን ጥቅም የለውም፡፡ መስማታችን ለጥቅማችን ይሁን፡፡ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ፍሬ እደሌለው ቃሉ ይናገራልና እንምሰለው፡፡





ሁለተኛው *በቂ አፈር የሌለበት ጭንጫ መሬት ነው፡፡* ከጭንጫው (ከድንጋይ) ከፍ ብሎ አፈሩ ስስ የሆነ ሲሆን በዚህ መሬት ላይ የተዘራው ዘር ይበቅላል፡፡ ነገር ግን ሥርን ስላልሰደደ በመሬቱ ላይ ቶሎ ይደርቃል፡፡ ይህም የሚያሳየን የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ደስ የሚላቸው ነገር ግን ለሰሙት ቃል ዋጋ ለመክፈል ያልተዘጋጁ ቅምጥልና ተላላ ሰዎችን ያሳያል፡፡

በቃሉ መኖር ትርፉ ለመንፈሳዊ ሰው እንጂ፤ በዚህ ዓለም ሐሳብ ለተያዙ ብዙ የማይመች ነገር አለው፡፡ ምክንያቱም፣ እነዚህ ሰዎች ፀሐይ (ስደት) ከረር ሲል መከራ ሲያጋጥም ቶሎ ማፈግፈግና መጠውለግን ያሳያሉ፡፡ ይኸም የሚሆነው እምነታቸው ልል መረዳታቸው ደካማና ዘላቂ ውሳኔ የሌላቸው ሰዎች ከመሆናቸው በላይ የመንግሥቱ ራዕይ የሌላቸው ናቸው፡፡

ክርስትና ዋጋ የምንከፍልበት እምነት ነው፡፡ ከዚህ እውነት ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይስማማል፡፡ "በእውነት በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡" (2ጢሞ. 3÷12፣ ፊሊ. 1÷25)፡፡ በአንድ ወቅት በቤተ ክርስቲያናችን ትከታተል የነበረች አንዲት ልጅ የእግዚአብሔርን ቃል ተካፍላ ከጉባኤያችን ስትወጣ የተመለከቷት ወላጆቿ ወደ ቤት ስትገባ ከቤታቸው

እንድትወጣ ተናገሯት፣ በዚህን ጊዜ በቀጥታ ወደ እኔ መጥታ እንዲህ አለችኝ ‹ሲያንቀለቅለኝ ጌታን ተቀብዬ ከቤት ተባረርኩ› ብላ አረፈችው፡፡ እኔም ክርስትና ብድራት ያለው ሕይወት በመሆኑ ዋጋ የምንከፍልበትና የምንሰደድበት እምነት እንደሆነ ለማስረዳት ብሞክርም በፍፁም አለች፡፡ እንዲያውም "እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አልመጣም" ብላ በዚያው ቀረች፡፡ ታዲያ ብዙዎች ክርስትናን እንዴት ይሆን የሚረዱት ይህ እንግዲህ በጭንጫ ላይ የተዘራው ዘር ሥር የሌለውና ስደትና ልዩ ልዩ መከራን የማይችል ቶሎም የሚጠወልግ ፍሬም የማይገኝበት ሰውን ያመለክታል፡፡

ሦስተኛው መሬት በእሾህ መካከል ያለው አፈር ነው፡፡ ይህ በእሾህ መካከል ያለው አፈር መልካም አፈር ሲሆን አፈሩም ጭንጫም አይደለም፤ ይልቁንም ለም የሆነ አፈር ነው፡፡ በዚህ አፈር የተዘራ ዘር ይበቅላል ደግሞም ያፈራል፡፡ ይህ እንግዲህ ከጌታ ጋር በመልካም ግንኙነት ህብረት የጀመሩ ሰዎችን ያሳያል፡፡ ነገር ግን በዚህ አፈር (ልብ) ውስጥ እሾኮችም አብረው አሉ፡፡ ይህም የዚህ ዓለም ሐሳብና ብልፅግ ነው፡፡ ታዲያ ይኸ ሰው ፍሬያማ እንዳይሆን በእሾህ ታንቆ ስለ ተያዘ የማያፈራ ሰው ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው ከቤተ ክርስቲያን ላይቀር፣





አገልግሎቱንም ሆነ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ላያስተጓግል ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍሬ የሚባል ነገር የለውም፡፡ ስለፍሬ በተሰጠው ትምህርት ውስጥ እንደተገጸው "... ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና" (ዮሐ. 15÷5)፡፡ እንደሚል መንፈሳዊ ክሳት የተጠናወተው ይሆናል፡፡

እንግዲህ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች መፀለይ፣ መስበክ፣ ወይም "ፓስተር" መሆን አይቻሉም ሳይሆን የሚለው ቃሉ፤ ፍሬ የላቸውም ነው፡፡ ይኸም ምንን ያመለክት ይሆን? በአጭሩ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ይፀልያሉ፣ ግን የሚጸልዩት ፀሎት ፍሬ የሌለው ነው፡፡ ቢሰብኩም በሚሰብኩት ስብከት የሚድኑ ወይም የሚታነፁ ሰዎች ግን አይኖሩም፤ ማለት መሆኑን መረዳት አለብን፡፡ ታዲያ በዚህ ዓለም የብልፅግና ሐሳብ የታነቀና ፍሬ ማፍራት ያልቻለ ሰው ፍፃሜው ምን ይሆን? የጌታ ቃል ሲናገር "ከእርሱም በእኔ ያለውን የማያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ቆርጦ ይጥለዋል፤" (ዮሐ. 15÷2) መጨረሻውም በእሳት መቃጠል ነው፡፡

አራተኛው መሬት መልካም አፈር ፍሬ የሚሰጥ ነዉ፡፡ ይህም የገበሬውን ድካም ከንቱ ያላስቀረበት አፈር (መሬት) ነው፡፡ ምንም እንኳን ፍሬ የሚያፈረው ከአራቱ መሬት አንዱ ቢሆንም መሬቱ ግን ብዙ ፍሬ የተገኘበት በመሆኑ ገበሬው ደስ የተሰኘበት ነው፡፡ "... እነዚህም ቃሉን ሰምተው

የሚቀበሉና ሠላሳ ሥልሳ መቶ ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው" (ማር. 4÷20) ይላል፡፡ ትክክለኛ የሆነውን የመንግሥቱን ሕይወት የሚገልጠው ይህ አራተኛው መሬት ነው፡፡ የክርስትና ሕይወት ለውጥና ዕድገት ባለሟቋረጥ ያለበት እምነት ነው፡፡ ስለዚህም በመልካም እርሻ □ተመሰለው አማኝ እነዚህ ፍሬ ይገለጡበታል፣ የመንፈስ ፍሬ (ገላ. 5÷22-22) የአገልግሎት ፍሬ (ዮሐ. 15÷8) የፅድቅ ፍሬ (ፊሊ. 1÷9-11) የንስሐ ፍሬ (ሉቃ 3÷8) ፡፡

### 1.2 የእንክርዳድ ምሳሌ (13÷29-33፤ 36-43)

የእንክርዳድ ምሳሌ ትርጉም ገበሬው (ክርስቶስ) በዓለም ላይ መልካም ዘርን ይዘራል፡፡ መልካም የተባለው ዘር አማኞች ናቸው፡፡ ሰይጣን (ጠላት) ደግሞ ክፉ ዘርን ማለትም እንክርዳድን ይዘራል፡፡ እንክርዳድም ስንዴውን ስለሚመስል ከስንዴው ጋር አብሮ ሲለሚያድግ አንዱን ከሌለው ለመለየት ቶሎ ይከብዳል፡፡

እንክርዳዶች ወይም ሐሰተኛ ክርስቲያኖችን (ማቴ.13÷36-43) ሰይጣን በዚህ ዓለም ላይ ይተክላል፡፡ ግን ለምን? ምስጥሩም እውነተኛ አማኞችን መንቀል ስለማይችል ነው፡፡ እንግዲህ መልካም ዘር የተባሉት አማኞች በተለያየ ሥፍራ ቢኖሩም ከእነርሱ ጋር የተቀላቀሉ እንክርዳድ የተባሉ ሐሰተኛ ክርስቲያኖች በኑሮአቸው የክርስቶስ አካል




የሆነችውን የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ያጠፋሉ፡፡ በዚህ ሁሉ ግን ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፣ይጠብቃል፡፡

ሰይጣን (ጠላት) በዋናነት ይህንን እንክርዳድ የሚዘራው የእግዚአብሔር ሰዎች ሲያንቀላፉና ልባቸው ከመትጋት ሲለግም ያን ጊዜ ለእርሱ ምቹ የሥራ ጊዜ ይሆንለታል፡፡ ቤተክርስቲያን በዓለም እስከ አለች ድረስ ክፋት፣ ዓመጽ አስመሳይ የሆኑ ክርስቲያናት፣ የስህተት አስተምሮና አስተማሪዎች ሰይጣን የሚልካቸው ወደ እውነተኛው ማሳ ሾልከው የሚገቡም፣ እንዳሉ ቃሉ ይናገራል (2ጴጥ. 2፣ 1ዮሐ. 4÷1-6)፡፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰዎች አእምሮ የሚዘራውን ክፉ ዘር የእውነትኛ ቃል በማስተማር ማውጣት የተሰጣት ትልቅ ኃላፊነት ነው (ራዕ. 2÷2፣ 24-25)፡፡ ነገር ግን በሰዎች ላይ ቶሎ መፍረድ ወይም አረምን መንቀል ለእኛ አልተሰጠንም፡፡ ይህም ስንዴንና እንክርዳድ መለየት በመጨረሻ መላዕክቶች ሊሰሩት የተሰጣቸው ሥራ ስለሆነ፡፡ የመንጋው እረኞች ግን ቅድስናዋን የጠብቀች፣ ለክርስቶስ ቀንም የተዘጋጀች ቤተ ክርስቲያን ለማቅረብ ግን መንፈሳዊ ትጋት ሊያሳዩ ይገባቸዋል (2ቆሮ.11÷2-6)፡፡ በዚህም ሂደት የእርምት እርምጃ መውሰድ በሥርዓት የማይሄዱትንም ማውገዝና እስከ ማግለል ድረስ መሄድ

ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህን ሲያደርጉ በፍቅርና በርኅራሄ መሆን አለበት፡፡

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዳነ፣ ያልዳነ፣ እውነተኛ ክርስቲያን፣ ሐሰተኛ ክርስቲያን ይኖራል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋው ወራት ሲያገለግል ከአስራ ሁለት ደቀመዛሙርቱ መካከል አንዱ የጥፋት ልጅ ይሁዳ (እንክርዳድ) ነበር፡፡ ስለዚህ በመንጋው ውስጥ በጎች ብቻ ሳይሆኑ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችም መኖራቸውንም ማወቅ ትልቅ ማስተዋል ነው (ማቴ.7÷15)፡፡ ስለዚህ መጠንቀቅ የኑሮአቸውን ፍሬናየ ትምህርታቸውንም ይዘት መመርመር አለብን፡፡ (ማቴ 7÷15-19፣ 1ቆሮ 4÷1-7)፡፡

እንክርዳድ ከስንዴ ጋር አብሮ ሲበቅል ምን ያደርጋል? ተፈጥሮ እንደሚያስተምረን የስንዴውን ምግብ በመሻማት ተክሉ እንዲቀጭጭ ብሎም ፍሬ እንዳይሰጥ ያደርገዋል፡፡ በእንክርዳድ የተመሰሉትም ሰይጣን (ጠላት) የዘራቸው ዘሮችም ቤተ ክርስቲያንን የማዳከመም፣ ምስክርነቷን የማጥፋትና ብርሃኗን ለዓለም እንዳይገለጥ ብርሃኗን መሸፈንና የምድር ጨውናቷን እንድታጣ ወደ አልጫነት የሚለውጥበት ሁኔታ አለ፡፡

በየዘመኑ ቤተ ክርስቲያን አቅም እንድታጣ የሚያደርጓት፣ ቅድስነዋንም የሚያጠፉ እነማን ይሆኑ?





የአገልጋይ ስም የያዙ ቃሉም እንደሚል ሐሰተኛ ሐዋሪያትና አስተማሪዎች አይደሉም (ይሁዳ 2-23)፡፡ የእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ትምህርትና ተግባር ስናይ የጥፋት ልጅ መሆናቸውን የሚያሳይ ብዙ ምልክቶች አሏቸው፤በትምህርታቸው መንጋውን በዘረኝነት ይከፋፍላሉ፣ ግብረ ሰዶማዊነትና ምንዝርናን ያስፋፋሉ፣ የትዳርን ክቡርነት በቃላቸውና በተግባራቸው ያጣጥሉ፤ ፍቺንም በመፈጸም የእግዚአብሔርን ቃል የሚሽሩ ግብዝ የሆኑና በአባታቸው በቃየል መንገድ በመሄድ ወንድሞቻቸውን የሚጠሉ ነፍሰ ገዳዮች፣ እንደ በለዓም ልባቸው በገንዘብ ፍቅር የታወሩ ናቸው፡፡

እውነተኛ ዘር በውስጣቸው ያለ ፤ የመንግስቱ ልጆች ግን የእግዚአብሔር ዘር ስለሆኑ፣ ፍጻሜያቸው በሙላት በሚገለጠው መንግስት ከክርስቶስ ጋር መንገስ ነው "ብንፀና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን" (2ጢሞ. 2÷12)፡፡

## 1.3 የሰናፍጭና የእርሾ ምሳሌ (13÷31-33)

የሰናፍጭ ምሳሌ፣ ሰናፍጭ በዚያን ዘመን ለነበሩ ገበሬዎች አነስተኛ ዘር ትባል እንጂ የተስተካከለ መሬት ካገኘች እስከ 3 ሜትር ያህል ወደ ላይ ልታድግ ትችላለች፡፡ በዚህም ሁኔታ ካደገች ከቁጥቋጦዎች በልጣ

በቅርንጫፉ ላይ ወፎች እስኪያርፉ ድረስ ትልቅ ዛፍ የመሆን ዕድል አላት።

የዚህ ምሳሌ ትርጉም ምን ይሆን? አንዳንድ ሰዎች ምሳሌውን ጌታ ኢየሱስ አሉታዊ በሆነ መንገድ ነው የተጠቀመበት ብለው ቢናገሩም፤ነገር ግን ቃሉ በቅድሚያ ሊያስተምረን ከፈለገው አንጻር ግን ወደዚህ ድምዳሜ እንድንደርስ አያደርገንም። ይልቁኑ ከፈሉ የእግዚአብሔር መንግስት ጅማሬ ምን እንደምትመስልና አስተዳደጓንም ለማመልከት በመሆኑ ምሳሌው አዎንታዊ ገጽታ አለው።

የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ከዘሮች ሁሉ ያነሰች ብትመስልም፤ ባደገች ጊዜ ግን በዓለም ግዛት ሁሉ እንደምትስፋፋና የዓለም ሕዝቦች በመንግሥቱ ውስጥ እንደሚያርፉ እፎይታንም እንደሚያገኙ፤ በመጨረሻም መንግሥታት ሁሉ የእርሱ መንግሥት እንደሚሆን የሚያሳየን ምሳሌ ነው። "የዓለም መንግሥት የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግስት ሆነች፤ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" (ራዕ. 11÷15) ።

የእርሾ ምሳሌ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙውን ጊዜ አሉታዊ የሆነ ትርጉም ይዞ ይገኛል፤ ይኸውም የግብዝነት (ሉቃ. 12÷1) የሥጋዊነት (1ቆሮ. 5÷6-8) የሐሰት





ትምህርት (ገላ. 5÷9) ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ማሳያ ሆኖ ቀርቧል።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጥር ለማስተማር በፈለገበት በዚህ ክፍል ግን ምሳሌው ሊያስረዳን የሚችለው እርሾው ለውጥንና እድገትን የሚያሳይ ሆኖ ነው የቀረበው።

እርሾ በሊጥ ውስጥ ገብቶ ሊጡን እንዲቦካና እንዲያድግ እንደሚያደርገው የእግዚአብሔርም መንግሥት ወደ ሰዎች ልብ ዘልቆ የሰውን ሕይወት እንደሚለውጥ፤ በእግዚብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አመላካች ነው።

የክርስትና ሕይወት ለውጥም ከውስጥ ወደ ውጭ እንጂ ከውጭ ወደ ውስጥ ወይም ውጫዊ አካሄድን ማሳመር እንዳልሆነ ወንጌል ያስተምረናል።

## 1.4 የተደበቀ ሀብትና የዕንቁው ምሳሌ (13÷44-45)

እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች አንድን እውነት የሚያሳዩና የሚያስተምሩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት እጅግ የከበረ መሆኑና ይኸንንም ለማግኘት ሰው ያለውን ሁሉ ሸጦ፤ የተደበቀ ሀብት ያለበትን እርሻና እጅግ ውድ የሆነ እንቁ የገዛ ነጋዴን ትመስላለች ይላል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች እርሱን ሲከተሉት አስቀድመው ሊተውት የሚገባውን ነገር ይናገራል። "ከኋላዬ

እንዲህ በማለት፡- “እርሱም ስለዚህም የመንግሥት ሰማያን ምስጢር የተረዳ ማንኛውም የኦሪት ሕግ መምህር፣ ከከበረ ሀብቱ ከምችት አዲሱንም አሮጌውንም የሚያወጣ ባለንብረት ይመስላል አላቸው” (ማቴ. 13 ፥52)።

በዚህ ምሳሌ መሰረት ደቀ መዛሙርቱ እራሳቸው አስተማሪ ለመሆን በጌታ እየተማሩና እየሰለጠኑ እንደሆነ ግልጽ ነው። ደግሞ አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት አይሁዳዊያን ከመሆናቸው የተነሳ የሕጉ ባለቤት ናቸው። አሁን ግን ጌታ የመንግሥቱን ምሳሌ ሲያስተምራቸው አዲሱን ትምህርት እየተቀበሉ በመሆናቸው የሁለቱም ሃብት ባሌቶች ሆነዋል። ይኸውም፣ የአሪት (የሕግ) እና የአዲሱን የመንግሥቱን ወንጌል። ስለዚህም ደቀመዛሙርት እንደ ጻሐፊ በመማርና በማስተማር ላይ እንደ ደቀ መዝሙር ምሳሌውን በመከተል በመኖር ቃሉን መተርጎም እንዳለባቸው በማሳሰብ የመንግሥቱን ምሳሌ ይጨርሳል።

# ምዕራፍ ሁለት

## “ለእናንተ የመንግሥት ሰማያን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤”

(ማቴ.13÷17)

## 2.3. የመንግሥቱ ወሰን፤

የእግዚአብሔር መንግሥት ሁሉንም ለእግዚአብሔር የምታደርግ አካል ናት፡፡ "መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች" (መዝ.103÷19)፡፡ እንደሚለው ቃል ሁሉንም መንግሥታት የሚታየውን የሰው መንግሥት፣ የማይታየውንም በመንፈሳዊ ዓለም የሚገኘውንም ዙፋናት የሚገዛ፤ በሥፍራ የማትወሰን የሰው ልጆች በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ የምትገኝ ገፅታዋ መንፈሳዊ መንግሥት ናት (ሉቃ.17÷20-21)፡፡

## 2.4. የመንግሥቱ ዜጋ መሆን፤

የእግዚአብሔር መንግሥት የራሱ የሆነ ዜጋ ያለውና ባለማቋረጥም ብዙ ዜጎች እንዲኖሩት የሚሠራ ነው፡፡ በዚህ መንግሥት ዜጋ ለመሆን ዳግመኛ በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ መወለድ ያስፈልጋል (ዮሐ. 3÷3-7፣ 1ጴጥ. 1÷23)፡፡

## 2.5 የመንግሥቱ ቋንቋ፤

ክርስቲያን በአንድ ጊዜ በሁለት መንግሥት ውስጥ ስለሚኖር በሥጋ በተወለደበት ወይም በሚኖርበት አገር ቋንቋ ይናገራል፡፡ ዳግሞም በመንፈሳዊ ገፅታ በመንግሥቱ ሥለተወለደ የተገኘበትን ዘርና ኑሮ እንዲሁም ቋንቋ ማንፀባረቅ ይጠበቅበታል፡፡ የመንግሥቱ ዜጋ ቋንቋ፡-





- ሰማያዊ ቋንቋ ይህም በልዩ ልዩ ልሳናት መናገር፤ የሚጠቅመውም እራሱን ለማነፅና ከእግዚአብሔር ጋር ምሥጥርን ለመነጋገር ነው፡፡ ይህ እንደ መንፈስ ፈቃድ ይሰጣል (1ቆሮ.12÷7-11፣ 14÷2-4)
- እንደ መንግሥቱ ቃል መናገር (1ጴጥ.4÷11)
- ሌሎችን የሚያንጽና የሚጠቅም ቃል መናገር (ኤፌ.4÷29)

## 2.6 የመንግሥቱ ሰንደቅ ዓላማ

የእግዚአብሔር መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ ያህዌ ንሲ የሚል ሲሆን ትርጓሜው እግዚአብሔር ዓላማዬ ነው ወይም በዓለማ በእቅድ የሚያራምድ አምላክ ማለት ነው (ዘፀ.17÷15-16)፡፡

ያህዌ ንሲ እግዚአብሔር ሕዝቡን በማንኛውም አቅጣጫ መምራት የሚችል መሆኑን ያሳያል፤ የመንግሥቱም ልጆች ሰንደቅ ዓላማ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሁሉንም ለእግዚአብሔር ክብር በማድረግ አኗኗራቸውን በምድር ይገልጣሉ (1ቆሮ.10÷31)፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች የንጉስ ጠባይ መግለጫዎች ናቸው፡፡ የመንግሥቱ ባሕል ምንድን ነው? "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅ፣ ሰላም በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ እንጅ መብልና መጠጥ አይደለችም" (ሮሜ14÷17-18)፡፡ እንዲሁም "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው" (ገላ. 5÷22) ይላል፡፡

የመንግሥቱ ዜጎች ሊንፀባረቅባቸው የሚገባው ጠባይ ወይም ባሕል ከላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ በምድር ላይ የትኛውም እውነትኛ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ እነዚህ ባህርያት ይኖሩታል፡፡ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ የመንግሥቱ ባሕርይ የያዘውን ዘር ዜጎቹ ይይዛሉ፡፡ በተፈጥሮ የብርቱካን ፍሬ ከብርቱካን ዘር እንደሚገኙ ሁሉ የመንፈስ ፍሬም ከመንግሥቱ ዘር (ከቃሉ) ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ የመንግሥቱ ዜጋ የሆነ ሁሉ የመንግሥቱ ገላጭ የሆነ ፍሬ መኖሩና መገለጡ የተለመደ ነው፡፡

የመንግሥቱ ልጆች የንጉሱን ባሕል የሚያሳዩ በመሆናቸው የፍቅር ባሕል፣ የደስታ ባሕል፣ የሰላም ባሕል፣ የበጎነት ባሕል፣ የእምነት ባሕል፣ የየዋህነት ባሕልና ራስን የመግዛት ባሕል አላቸው፡፡ በምድር የእግዚአብሔር መንግሥት ገላጭ ስለሆኑ ዜጎቹ በጨለማ ያለው መንግሥት





ልጆች ባሕላቸውን ተመልክተው አንተ ከዚህ መንግሥት (ከዓለም) አይደለህም ይላሉ፡፡

## 2.10 የመንግሥቱ አገልጋዮች

እግዚአብሔር መንግሥቱን የሚያውጁለት ልዩ ልዩ አገልጋዮች አሉት፡፡ እነሱም "አንዳንዶች ሐዋርያት አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎች ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው" ኤፌ.4÷11 ይላል፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ጥሪ (ተልዕኮ) ያላቸው አገልጋዮች በመንግሥቱ ውስጥ የሚሰሩት ትልልቅ ሥራዎች አሉ፡፡ ይህም፡-

- የብልሃተኛ አናፂ ሥራ (1ቆሮ.3÷9-10) የመንግስቱን ዜጎች የንጉሱ መገለጫ ሕንፃ አድርጎ መሥራት፡፡
- የትጉ ገበሬ ሥራ (1ቆሮ. 9÷10-11) መንፈሳዊን ዘር መዝራት በመንግሥቱ እርሻ ላይ (1ቆሮ. 3÷10) መከሩን ማብዛት፡፡
- የወታደር ሥራ (2ጢሞ. 2÷4) ሰዎችን ከጨለማው አገዛዝ ለማውጣት እየተጋደሉ (ኤር.6÷10-18) መንግሥቱን ግዛቱን በሰው ልብና በምድር ማስፋት፡፡

የመንግሥቱ አገልጋዮች የሚሠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ፤ ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልን በመቀበልና በማሄዱበት ሥፍራ ሁሉ ንጉስ ከእነርሱ ጋር ስለሆነ ውጤታሞች ናቸው (ማቴ.28÷19-20፣ 1ቆሮ. 3÷9፣ የሐሥ. 1÷8)፡፡

## 2.11. በመንግሥት ውስጥ የሚፈፀም ወንጀሎችና ቅጣት

ንጉሱ በመንግሥቱ ዜጎች ላይ ሙሉ መብትና ስልጣን አለው፡፡ ከመንግሥቱ መርህ የወጡ ዜጎች ሲኖሩ የሚወነጀሉበትና የሚቀጡበትም ሥፍራ ናት የእግዚአብሔር መንግሥት፡፡ መተዳደሪያው ደንብ እንደሚናገረው "ነገር ግን ጌታ በሚፈርድብን ጊዜ ስንገሠጸበን፤ ይኸውም ከዓለም ጋር ስብረን ስንዳንኩነን ነው" (1ቆሮ.11÷32) በማለት፡፡ የመንግሥቱ ልጆች ይቀጣሉ የሚቀጡት ግን በሰሩት ኃጢአት ንስሐ እንዲገቡ ነው (2ቆሮ.7÷10)፡፡ ባሕሪውን በመምሰል ሊያድጉ ይጠበቅባቸዋል (ዕብ.12÷7-17)፡፡ ቅጣቱም ደረጃ አለው፤ ይኸውም በስጋ፣ መድከም፣ መታመምና ያለጊዜው መሞት (1ቆሮ. 11÷30፣ 1ዮሐ. 5÷16-17) የሚያስከትል ነው፡፡

### ቅጣት የሚያስከትሉ፣ ወንጀሎች

- ➢ ወንድምን መጥላት (1ዮሐ. 3÷11-15) ለሞት የሚያደርስ ቅጣት፡፡





- ➢ የይቅርታ ሕይወት ማጣት (ማቴ. 18÷21-35) ይቅር ያለመባል ቅጣት፡፡
- ➢ የድፍረት ኀጢአት (1ቆሮ. 5÷1-5) ከመንግሥቱ ጥበቃና ከለላ ውጭ መሆን፡፡
- ➢ የክርስቶስን አካል መከፋፈል፣ በቅናት፣ በክርክር በሥጋዊነትና በልዩ ልዩ እንግዳ ትምህርት (1ቆሮ.3÷16-17) ይህ ከባድ ወንጀል ስለሆነ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፡፡
- ➢ የሥጋ ሥራ (ገላ.5÷19-21) እነዚህን የሚያደርጉ መንግሥቱን አይወርሱም፡፡

የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት ዜጎቹ በትክክለኛው መርህ በመሥራት የንጉስን ባህልና አኗኗር በማንፀባረቅና የተሰጣቸውን መብትና ግዴታ በማወቅ ይመላለሱ ዘንድ የተሰጣቸው ሕግ ነው፡፡

የመንግሥቱ ዜጋ የሆነ ሰው የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ፣ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በመያዝ በጨለማው መንግሥት ላይ ተፅዕኖ ማምጣትና በክፉ አገዛዝ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በወንጌል እውነት ነፃ በማውጣት የመንግሥቱ ዜጎችን ማብዛት ይጠበቅበታል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## “የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ...”

# 3

## የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል

ወንጌል የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ነው፡፡ በወንጌል ስብከት አምነው የሚድኑ ሁሉ በመንግሥቱ ቃል ይወለዳሉና የመንግሥቱ ልጆች ተብለው ይጠራሉ፡፡ "ጥሩው ዘር የእግዚአብሔርን መንግስት ልጆች ያመለክታል" (ማቴ. 13÷38) ይላል፡፡

የመንግስቱ ቃል የሚወክለው ራሱን እግዚአብሔርን ነው፡፡ የወንጌል አገልግሎት ክቡር የሆነው በሰዎች ልብ ውስጥ የራሱን የእግዚአብሔርን ዘር መዝራትና ሰዎችን ከእርሱ ጋር ማዛመጃ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ምን ምን ይዟል? እስቲ ይህንን ሃሳብ በዝርዝር እንይ፡-

### 3.1 የመንግሥቱ ቃል የእግዚአብሔርን ዘር በውስጡ ይዟል፡፡

"ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ" (1ጴጥ. 1÷23)፡፡

በዘር ውስጥ የሚተላለፈው የቤተሰብ ባህሪና ሕይወት እንደሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርን ዘር የተካፈሉ ሁሉ የእርሱን ባህርይና ሕይወት ይይዛሉ፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርጎ ማመንና መቀበልን ዳግመኛ መወለድና የማይጠፋ የእግዚአብሔርን ዘር መያዝ እንደሆነ አበክሮ ይናገራል፡፡ ቅድሚያም ቢሆን አዳም ሲፈጠር የያዘውን የእግዚአብሔርን ዘር፣ መልክ፣ ምሳሌና እስትንፋስ እንደሆነ በማያሻማ መልኩ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ዘፍ.1÷26-28፣ 2÷7)፡፡ እንግዲህ በክርስቶስ ማመን ማለት ከእርሱ ዳግመኛ መወለድ ከሆነ፤ ፊተኛው ሰው አዳም ከእርሱ ከእግዚአብሔር ተወለደ ብንል ይኸ ስህተት ይሆን? በርግጥ የአማርኛው ትረጉም "ተፈጠረ" ቢልም የዕብራይስጡ ትርጉም ግን ተወለደ እንደሚል ቋንቋውን የሚያውቁ ይናገራሉ፡፡

የመንግሥቱ ቃል አዲስ ሕይወትን የሚሰጥና መለኮታዊ የሕይወትን መርህ በውስጣችን የሚያደርግ ነው፡፡ ሁሉም ፍጥረት እንደ ተገኘበት የዘር ዓይነት ያድጋል፣ ይኖራል፡፡ የእግዚአብሔርንም ዘር የያዘ እንዲሁ የተገኘበትን መንግሥት ኑሮ በመኖርና ለፍጥረትም በመግለጥ ከማን ወገን መሆኑን ያሳያል፡፡





በርግጥ በልማዳዊ ኑሮና በሰዎች ወግ ለተተበተበ ሰው አሁን እያልነው ያለው ሐሳብ ጆሮን የሚያሳክክና ለማመን የሚያስቸግር ነገር ቢመስልም፤ እውነቱ ግን የተወለድንበት ቃል የመንግሥቱ ልጆች ሆነን፤ የመንግሥቱን ኑሮ ለመኖር እንደሆነ መጽሐፍ ያስተምራል፡፡ ይኸም፣ የመንግሥቱ ቃል የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ፣ የማይጠፋ ሕያው ዘርና የመንግሥቱ ነፀብራቅ (ገላጭ) ለዜጎች ያደረገ መሆኑን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡

### 3.2 የመንግስቱ ቃል የመንግስቱን የኑሮ መርህ ይዟል፡፡

"ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡" መዝ. (119) ÷105

የእግዚአብሔር መንግሥት ሕዝብ የሚተዳደርበት ከራሱ ከንጉሱ የተሰጠ ሕግ አለው፡፡ አንድ ሀገር እንደ ሀገር ለመመራት የራሷ ሕግ-መንግሥት እንዳላት ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ልጆችም የሚመሩበትና የሚተዳደሩበት ሕግ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እዚህ ላይ የመንፈስ ቋታችን ከቻለው ሕጉ በተቀበልነው ሕይወት ውስጥ አለ ብንል የተፃፈውን ቅዱስ ቃሉን ይዘን ነው፡፡

የተቀበልነው ሕይወት የሕይወት መንፈስ ሕግ የሚሠራበት ነው፡፡ "በክርስትስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ

...” (ሮሜ 8÷2)ይላል፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ስላለን የሚሰራብን ባለማቋረጥ የሕይወት መንፈስ (ሕይወት ሰጪ መንፈስ) ሕግ ነው፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ዮሐንስ “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢያትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢያትን ሊያደርግ አይችልም፡፡” ያለው (1ዮሐ.3÷9)፡፡ በዚህ ክፍል በግልፅ እንደተቀመጠው “ኀጢአትን አያደርግም” እና “ኀጢአትን ሊያደርግም አይችልም” የሚለው በውስጡ የእግዚአብሔር ዘር ኀጢአትን የሚቃወም፣ ዓመጽንም የሚጠላ ስለሆነ ነው፡፡

በውስጣችን የምንካፈለው ዘር መንግሥቱ የሚፈልገውን የጽድቅና የቅድስና ኑሮ መኖር እንድንችል የሚያደርግ ነው፡፡ “አንድ ወንድም በአንድ ወቅት በጌታ በተሰወጠበት ጊዜ ላይ በቤተክርስቲያን የሚሰጠውን የደቀመዝሙር ትምህርት ሳይጀምር ኀጢዓት የሆነውንና ጽድቅ ያለበትን ነገር ከዕውቀት በፊት እንደተረዳ መናገሩን አስታውሳለሁ፡፡” ይኸም የሚያሳየው በተካፈለው ዘር ውስጥ ክፉውን ከመልካም እንድንለይ የሚያስችል ሕግ መኖሩን ነው፡፡ በውስጣችን የተተከለው ቃል እንዴት መኖር እንዳለብን መመሪያን የሚሰጠን ነው፡፡

ሁለተኛው የተፃፈልን ቃል ነው፡፡ ይኸም የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ “የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ





ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅ ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል” (2ጢሞ. 3÷16-17) ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ዜጎቹን ብቁ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ቃሉ ለትምህርት፣ ለተግሳፅ ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅ ላለው ምክር ይጠቅማል የሚለው፡፡ የመንግሥቱ ቃል ጠቃሚ ነው፡፡ በተለይ በዚህ ዘመን በነገር ሁሉ የበቃ ምሳሌ የሚሆን ትውልድ ለማፍራት የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ለማንበብና ለመማር ጊዜ የሚሰጡ ሰዎች ያስፈልጉናል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል፤ ማንበብ ማለት አንድን መጽሐፍ እንደ ማንበብ አድርገን ማሰብ የለብንም፤ ይልቁኑ ቃሉ አካል እንዳለው ሰው ስናነበው የሚናገረኝን ሰማሁ በሚል መንፈስ ልናነበው ካልቻልን ከሌሎች መጽሐፍ ለእኛ አልተለየም፡፡ ስለዚህ ቃሉ አስተማሪ ሆኖ የሚያስተምረን፣ መካሪ ሆኖ የሚገስጸንና ጠማማውን ልባችንን የሚያቀና መሆኑን ልንረዳ ይገባል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ (የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል) የሐይማኖተኞች መጽሐፍ አይደለም፡፡ ሕይወት ለዋጭ የንጉስ ሕግና መሻቱን (ፍላጎትን) የያዘ ቃል ነው፡፡
“... ከአፌ የሚወጣው ቃል እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል...” (ኢሳ. 55÷11)፡፡ የእግዚአብሔር ቃል

ለእኛ መሻት አይገዛም፤ ይልቁኑ የእኛን መሻት ይገዛል እንጂ። የእግዚአብሔር ቃል ከእግዚአብሔር የተላከ ቃል ነው። የተላከበትን ዓላማ በህዝቦቹ እና በምድር ላይ ይፈፅማል እንጂ እንዲሁ ወደ እርሱ አይመለስም። ይኽ ቃል በውስጣችን የሚያደርገው የእግዚአብሔርን መንግሥት መሻት መማር ነው። ደግም ግልፅ የሆነ መመሪያ ለመንግሥቱ ዜጎች ያሳያል፤ ያስተምራል።

### 3.3. የመንግሥቱ ቃል ዓለምን የሚገዛ ጥበብ ይዟል፤

"ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል"መዝ (119) ÷72

በዓለም ላይ ውድ ነገር ቢኖር ጥበብ ነው። ጥበብ ከወርቅ ከዕንቁ ይበልጣል። ጥበብ ገንዘብ፣ ንብረትና ሐብትን ያመጣል። ንግስት ሳባ ጥበብን ከእግዚአብሔር የተቀበለውና ዝናው በምድር ሁሉ ላይ የናኘው ንጉስ ሰለሞንን ለማየት በሄደችበት ጊዜ የተናገረችው እንዲህ ብላ ነበር "በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎች እነዚህ ባርያዎችህ ምስጉኖች ናቸው" (1ነገ.10÷8)። እንግዲህ ንግሥቲቷ ከምንም ነገር በላይ እነዚህ ጥበብህን የሚሰሙ ባሪያዎች ምስጉኖች ናቸው በማለት በመደነቅ ትናገራለች ።

በቀደመው ኪዳን የንጉስ ሰለሞን ጥበብን ለመስማት ሰዎች ከተለያየ ሥፍራ ዋጋ በመክፈል ይመጡ ነበር።





ነገር ግን በዚህ በተሻለ ኪዳን ውስጥ የምንገኝ የጥበብ ምንጭ የሆነውን አምላክ ራሱኑ የምንሰማበት ጊዜ ውስጥ ነው ያለነው። እግዚአብሔር ለዓለም ጥበቡን ገልጧል። የእርሱ ጥበብ የጸደቀበት ሰው ጠቢብ፤ ጥበቡን ያቃለለ ደግሞ ሞኝ መሆኑን ቃሉ ይናገራል።

ለመሆኑ የእግዚአብሔር ጥበብ እንዴት ተገለጠ? "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ሐይል ነው።" (1ቆሮ.1÷18)። የመስቀሉ ቃል ዓለምን ለማዳን የተገለጠ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። "የእግዚአብሔር ሐይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።" (1ቆሮ. 1÷24)። ምንም እንኳን ዓለም የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል የተገለጠበት ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ ብትቆጥረውም። ለእኛ ግን ለምንድን የእግዚአብሔር ማዳን ያለበት ሃይል እንደሆነ እንመሰክራለን። ታዲያ ለምን ይህ ጥበብ ሞኝነት ተባለ? "መቼም አይሁድ ምልክት ይለምናሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ እኛግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካን ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው..." (1ቆሮ.1÷22-23)።

ለአይሁድ መሲሁ በመስቀል የመሰቀሉ ጉዳይ የማይታሰብ ነው። ለምን? እንዲህ ዐይነቱ ሞት ?እርጉም ሰው ሞት ነውና (ገላ 3÷13)። ለአሕዛብ (ለግርክሰዎች) ደግሞ ምውት ካልሆኑ አማልክቶች መካከል አንዱ በሰዎች

መካከል ተገኝቶ ሞትን ቀመሰ ማለት ተላላነትና ሞኝነት ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈላቸው መልዕክት ውስጥ የቆሮንቶስ ሰዎች አይነተኛ ችግር የአእምሮ ትምክህት የኃጢአት ባሕርያቸው ነበር፡፡ ለዚህም ነው "ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና" በማለት የጻፈው፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን የተጠቀመበትን መንገድ ስናይ አስገራሚነቱ ከመጠን ያልፋል፡፡ ይኸውም ሰዎች ሞኝነት በሚሉት በውርደትና በድካም የተገለጠ የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ነው፡፡ ለዚህም ነው ለመዳን የመስቀሉን ቃል ለመረዳት በአእምሮ ሞኝ መሆን የሚያስፈልገው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወቱና የአገልግሎቱ ማዕከል የሆነው የክርስቶስ መስቀል ነበር፡፡ ቃሉም እንዲህ ይላል "በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና" (1ቆሮ. 2÷2)፡፡ በዚህ ስብከቱ ሐዋርያው አንድ አቅጣጫ ይዟል ይኸው "የተሰቀለውን ክርስቶስን"፡፡ ግን ለምን ይሆን ወደ እዚህ ውሳኔ የደረሰው? በአጭሩ በዚህ መልዕክት ውስጥ የድነት መንገድ ስላለ ነው፡፡ "በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን" (1ቆሮ. 1÷21) ይላል፡፡ ስለዚህ ወንጌል ሰው በአእምሮው ተጠቦና ተፈልስፎ የመጣው ባለመሆኑ ለፍጥረታዊ ሰው





ሞኝነት ይመስላል፡፡ ነገር ግን የእግዚብሐርን የድነት ዕቅድ የያዘ ቃል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለመልዕክተኞቹ በሚሰጠው መንፈሳዊ ሙቀት (ኃይል) ወደ ሰዎች ሁሉ መድረስ የሚገባው መልዕክት ሲሆን በተገለጠው በእግዚአብሔር ጥበብ ዓለምን የሚማርክ ነው፡፡

እንግዲህ ወንጌል (የእግዚአብሔር የመንግሥት ቃል) የሰዎችን የዘላለም አድራሻ የሚለውጥ የማዳን ኃይል የያዘ ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልዕክት እንዲህ በማለት ገልጾታል፣ "የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" (2ቆሮ.4÷4) በማለት፡፡ ይህ የክብር ወንጌል(የመንግሥቱም ቃል) የሚሰበከው ሰዎችን ወደ ክብር ለመጥራት ነው፡፡ ቃሉም እንዲህ ይላል፡- "... ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩ ስለጠራችሁ..." (1ተሰ.2÷11-12)፡፡ ወንጌል የህያው የእግዚአብሔር የመንግስቱ አካልና ለእርሱ የተለየ የክብር እቃ እንጂ የልማዳዊ ህይወት እስረኛ አያደርገንም፡፡

**ምሥራቹ አሁት**

“እኛ ግን አገራችን (Citizenship) በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠብቃለን፡፡

(ፊሊ. 3፥20)

# 4

## የመንግሥቱ ዜጋ

ዜጋ በአንድ ሃገር ውስጥ በመወለዱ ወይም ፈቃድ በማግኘቱ የተወላጅነት መብት ያለው ሰው ማለት ሲሆን፤ ዜግነት ደግሞ በአንድ ሃገር ውስጥ በተወላጅነት ወይም በፈቃድ የሚገኝና ሰውዬው የዚያ አገር ሰው የመሆኑ መግለጫ ነው፡፡ ሃገር በውስጡ ሕዝቦች የሚኖርበት የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ያለውና በአንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ስር የሚገኝ ግዛት ነው፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለፊልጵስዮስ ሰዎች የጻፈላቸው መልዕክት ላይ የአማርኛው ትርጉም "እኛ አገራችን በሰማይ ነው" ሲል የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ይህንኑ ቃል "citizenship" ወይም ዜግነት በማለት ይገልጸዋል፡፡ የመዝገበ ቃላት ትርጉም እንደሚያሳየው "ሃገር" ከመልከዓ ምድሩ ክልል (ግዛት) ጋር ሲያይዘው፤ "ዜግነትን" ግን በአንድ ሃገር ውስጥ የተወለደን ወይም ፈቃድ በማግኘቱ የዚያ ሃገር ሰው መሆን በማለት ይገልጸዋል፡፡ እንግዲህ የእንግሊዘኛውን ቃል ትርጉም በመያዝ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሁሉ

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ (ሰማያዊ ፍጥረታት) ናቸው ማለት እንችላለን፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት ዜጋ መሆን በምድር የአንድ አገር ዜጋ ከመሆን በላይ ላቅ ያለና አእምሮ ሊቀምረው የማይችል መብትና ጥቅሞች እንዲሁም የኑሮ ግዴታዎችም የአሉበት ነው፡፡ በቅድሚያ እንዴት የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መሆን ይቻላል? የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ለመሆን ዳግም መወለድ ያስፈልጋል፤ ይህም ድርጊት የሚከናወነው በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ነው፡፡ ዳግም መወለድ ካገኘንበት ቅጸበት ጀምሮ የመንግሥቱ ልጆች ወይም ዜጋ ተብለን እንጠራለን (ማቴ.13÷38)፡፡ የመንግሥቱ ዜጋ የሆነ ሰው የሚያገኘው ጥቅም ምንድ ነው? እስኪ በተወሰነ መልኩ ለማየት እንሞክር፡-

- የዘላለም ሕይወት (ዮሐ.3÷16) ይህ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበትና በኅብረት መኖር ማለት ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡፡ ደግሞም የተዘጋጀችው በክርስቶስ ነው (1ዮሐ.5÷20)፡፡ ክርስቶስን በማመን የምንቀበለው በወደፊት ሕይወት ብቻ ሳይሆን በአሁን ጊዜ የምናገኘው ነው፡፡ ያም ሕይወት ራሱ ክርስቶስ ነው (ዮሐ.17÷3)፡፡





- የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል (ኤፌ.2÷19) ቤተ ሰብ ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ዝምድና መኖሩን ያሳያል፡፡ አማኞች በዓለም ላይ እንግዶችና ምጻተኞች ሲሆኑ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ግን የንጉሱ ቤተሰብ ናቸው፡፡
- የክርስቶስ ሰላም (ኤፌ.2÷14፣ ዮሐ.14÷27) ሰላም የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ሻሎም" ሲሆን የሚያመለክተውም፣ መልካም ጤና፣ ሀብት፣ ጥበቃ እና መልካም ግንኙነትን የሚያጠቃልል ሙሉ ነገር ነው (ኢሳ. 26÷1-4፣ መዝ. 29÷11፤)፡፡ ክርስቶስ ሰላማችን ነው፤ ሲባል የእነዚህ ሁሉ ዝርዝር ነገሮች ተጠቃሚ መሆናችን ያሳያል፡፡
- ልጅ መሆን (ዮሐ.1÷12-13) ልጅነት ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ በመወለድ ያገኘነው መብት ነው (ሮሜ 8÷15-17፣ ገላ.4÷5-7)፡፡ ይህም የእግዚአብሔር የፍቅር ጥጉን ያሳያል (1ዮሐ.3÷1)፡፡ ልጅ መሆን በሌላ መልኩ ልጅ የሆኑለትን ባሕርይ መውረስን፣ መያዝን ያሳያል (ኤፌ. 2÷2፣ 5÷8)፡፡
- የመንግሥቱ ወራሽ መሆን (ማቴ. 25÷34) የመንግሥቱ ዜጋ ሲወለድም የርስት ወራሽ ሆኖ ነው የሚወለደው (1ጴጥ. 1÷3-5፣ ገላ. 4÷7)፡፡ ስለዚህም ዜጎች

የተዘጋጀላቸውን ሰማያዊ በረከት በአሁኑ ጊዜም ወርሰዋል፤ ወደፊትም በሚመጣው ዓለምም ይወርሳሉ፡፡ እንግዲህ ዜጋ መሆን እነዚህንና በዚህ ያልተገለጡ ብዙ ጥቅሞችን ይዟል፡፡

ከሁሉ በፊት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስንገባ የምናገኘው የማንነት እና የሕይወት እንጂ የሃይማኖት ለውጥ አይደለም፡፡ አንዳንዶች ክርስትናን በዓለማችን ላይ እንዳሉ የሃይማኖት ክፍል አድርገው ቢቆጥሩም ዐይኑ የተከፈተለት (መለኮታዊ ብርሃን ያገኘ) ሰዉ ግን መንግሥት እንደ ለወጠና የመንግሥቱን ሕይወት እንደ ተካፈለ መንፈስ በሰጠው ዕውቀት ይህን ይረዳል፡፡ በአንድ ወቅት በአንድ ትልቅ ክሩሴድ በተደረገ የወንጌል አገልግሎት ላይ የደህንነት ጥሪ ሲደረግ አንድ በዓለማችን ላይ የታወቀ የፊልም አክተር ወደ ፊት መጣና የንስሐ ፀሎት አደረገ፡፡ ይኸ ሰው ታዋቂ ስለነበር ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲመሰክር ተጠየቀ፤ እርሱም እንዲህ አለ፦ "እስከ አሁን ሁለት እምነት ብቻ ነበረኝ አሁን ግን ሶስተኛ ሃይማኖት ስላገኘሁ ደስብሎኛል" ብሎ ተቀመጠ፡፡ እንግዲህ ይህ ሰው እውነተኛ መገለጥ አለማግኘቱን ልብ በሉ፡፡

አዲስ ፍጥረት በመሆን ወደ ብርሃን መንግሥት ስንቀላቀል ራሳችንን የምናገኘው በክርስቶስ ውስጥ ነው፡፡





ይህ እንግዲህ በፊተኛው ሰው የነበረውን ወደ ኋለኛው አዳም ወደ ክርስቶስ በመጨመር ከእርሱ መወለድን ያሳያል፡፡ ፊተኛው አዳም፣ የሰው ዘር በኃጢያቱ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ እንዲሆን ያደረገና ሞትን ያወረሰ ነው (ሮሜ 5÷15)፡፡ ሁለተኛው አዳም የሰው ልጅ በመባል የተጠራው ጌታ ኢየሱስ ግን ሰው በእግዚአብሔር ፊት በኃጢያቱ ተጠያቂ እንዳይሆን ዕዳውን የከፈለና የዘላለም ሕይወት ወራሽ ይሆን ዘንድ ያደረገ መሆኑን ቃሉ ይናገራል (ሮሜ. 5.15-17)፡፡

ከእግዚአብሔር መወለድ የሚያደርገን መንፈሳዊ ሰውና የመንግሥቱ ዜጋ መሆን እንደሆነ ተመልክተናል፤ ቃሉም "ከስጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው" (ዮሐ. 3÷6) በማለት፡፡ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ዘር (መለኮታዊ ዘር) በመያዝ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ ያስችለናል፡፡ ደግሞ ከተገኘንበት ዘር የተነሳ በምድር ላይ እግዚአብሔራዊ ሕይወት የመኖር ኃላፊነት አለብን፡፡

በምድርም ሆነ በሰማይ ዜጋ ስንሆን ዜጋ በሆንበት መንግሥት ውስጥ የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎች እንዳሉብን የታወቀ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን በምድር ዜጋ በሆንበት መንግሥት ያለንን መብትና ግዴታ እዚህ ላይ

ማንሳት እንተውና ሰማያዊ ዜጋ የሆነ ሰው ኃላፊነቶች እንመልከት፡፡ ኃላፊነታችን ምንድ ነው? መቼም ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም የተወሰኑትን ግን እንይ፡-

- የክርስቶስ እንደራሴ (አምባሳደር) መሆን፤

"ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤" (2ቆሮ. 5÷20) ፡፡

አምባሳደር (እንደራሴ) የአገሩ ወኪል በመሆን በሌላው አገር የሚመደብ ባለስልጣን ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎችም በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪሎች በመሆን ይኖራሉም ይሰራሉም፡፡ ሥራችንም በዋናነት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን መለመን ነው፡፡ ስለዚህም መንግሥቱን የማስተዋወቅና የመንግሥቱን መልዕክት የማቅረብ ኃላፊነት ከጌታ ተቀብለናል፡፡ ቃሉም እንዲህ ይላል፤ "እግዚአብሔር በእኛ እማካይነት ጥሪውን ያቀረበ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን" (2ቆሮ. 5÷20) ፡፡

ሰው በኃጢያቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር የራቀና ለጨለማው መንግሥት ተገዢ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ርቀት በሃሳቡ መኮብለሉና ከእርሱ መለየቱ እንጂ በአካል መሰወሩን አያመለክትም፤ አምላካችን ሰማይንና ምድርን የሞላ በመሆኑ፡፡





ወንጌል የጠፋውን ሰው የሚፈልግ የዕርቅ መልዕክት ይዟል፡፡ ዜጎች የሚናገሩት የወንጌል መልዕክት በአጭሩ ይህን ይመስላል "...ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሳ..." (1ቆሮ.15÷3) የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ወደዚህ መንግሥት ለመግባት ንስሃ ይገቡ ዘንድ ወንጌል ይሰበካል፡፡ "ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ..." (ማር.1÷14-15)፡፡

የመንግሥቱ ወንጌል የፈጠራ ታሪክ አይደለም፡፡ ይልቁን የሰውን `ሕይወት የሚለውጥ ሕያው መልዕክት እንጂ፡፡ "ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት የወሬ ጉዳይ ሳይሆን የሀይል ጉዳይ ነው" (1ቆሮ. 4÷20) ይላል፡፡ እንግዲህ መንግሥቱን በኃይል የማስፋትና የማስተዋወቅ ተልዕኮ ለዜጎቹ ሁሉ ተሰጥቷል፡፡

- የመንግሥቱ ካህናት

"ለወደደን ከኃጢያታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድንሆን ላደረገን...." ራዕ.1÷6

ካህናት በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆሙ አገልጋዮች ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን ይህ ሃይማኖታዊ አገልግሎት ለሌዊ ዘር የተሰጠ ሲሆን፤ ነገር ግን ከሃይማኖታዊ ሥርዓት ጋር ሳይያያዝ የእስራኤል ሕዝብ

ሁሉ ካህናት ተብለው ይጠሩ እንደ ነበር ቃሉ ይናገራል (ዘጸ.19÷5-6)።

በብሉይ ኪዳን የነበሩት ካህናት ይሰጡት የነበረው አገልግሎት የእግዚአብሔርን ሕግ ለሕዝቡ ማስተማርና ልዩ ልዩ መስዋዕቶችን በማቅረብ ሕዝቡንና እግዚአብሔርን ማገናኘት ከዋና ዋና አገልግሎታቸው መካከል የሚጠቀስ ነው (ዕብ. 8÷3፣ ዘጻ. 27÷9-10፣ 31÷9-13፣ 33÷10) ።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ የንጉስ ካህናት የሚባሉት በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑና ዳግም የተወለዱ ሰዎች ናቸው (1ጴጥ. 2÷9-10፣ 5÷9-10) ። ስለዚህም የመንግሥቱ ዜጋ የሆነ ሁሉ ካህናት ስለሆኑ የአምልኮ መስዋዕት ለእግዚአብሔር በእውነትና በመንፈስ ያቀርባሉ (ዮሐ.4÷24) ። ደግሞም የንጉሱን ሥርዓት፣ ወግና ሕግጋት በጨለማው ግዛት ላሉ ሁሉ ያስተዋውቃሉ። በዚህ መንገድም እግዚአብሔርንና የጠፋውን የሰውን ልጅ ያስታርቃሉ።

☞ የመንግሥቱ ወታደር

"እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ስጦር የአከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።" (2ጢሞ.2÷5-6)

የመንግሥቱ ዜጋ የክርስቶስ ወታደር ነው። ወታደር በጦር ሰራዊት ውስጥ ገብቶ የሚያገለግል መለዮ ለባሽ





ነው። ክርስቲያንም በዚህ ዓለም ሲኖሩ መለዮውን ወይም የጦር ዕቃውን ታጥቆ እንዲኖር ቃሉ ያዛል "የእግዚአብሔርን የዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ" ኤፌ.6÷11። ወታደሮች በምድር ላይ ያሉ ሃገራቸውን የሚወክል ልብስ እንደሚለብሱ፤ የመንግሥቱም ዜጎች የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወክል ልብስ ይለብሳሉ። ዜጎቹም ጠላት ስላለባቸው ባለመቋረጥ በውጊያና በመንፈሳዊ ተጋድሎ ውስጥ ይገኛሉ (ኤፌ. 6÷11-12)። ጠላታቸው ግን ሥጋና ደም ሳይሆን የክፉ መንፈሳዊ ሰራዊቶች ናቸው። ስለዚህም የጦር ዕቃቸው ወይም መሳሪያቸው መንፈሳዊ ነው (2ቆሮ. 10÷3-4፣ ኤፌ. 6÷10-18)። የሚጋደሉትም በሰው ሃሳብ ውስጥ የመሸገውን ምሽግ ለማፍረስና የሰውን ሁሉ አእምሮ ለክርስቶስ እንዲታዘዝ ለመማረክ ነው።

☞ ዜጎች የሚያሳዩት ኑሮ (ባሕል)

ኑሮ አንድ ሰው በዕድሜ ዘመኑ የሚያሳልፈው ሕይወት ማለት ነው። የክርስተና ኑሮ የክርስቶስን ሕይወት በምድር በአኗኗራችን መግለጽ ወይም ማሳየት ማለት ነው። የዜጎቹ ኑሮ ከግንዱ የሚወጣና እንደ ቅርንጫፍ ፍሬውን እንደሚገልጥ፤ የክርስቶስን ባሕርይ ለዓለም ሁሉ መግለጥ ጥሪያቸው ነው (ዮሐ.15÷1-11)። የመንግሥቱ ኑሮ በፍሬ

መገለጡ ሕያው ግንኙነት ከጌታ ጋር ማድረግንና መኖሩን ያሳየናል፡፡

የመንግሥቱ ሕይወት የዜጎቹ ባሕርያት፣ ጠባይና ግብር ነው፡፡ በመንግሥቱ ውስጥ እኛ እንድናጸባርቃቸው የሚጠበቅብን መለኮታዊ ባሕርይት አሉ፡፡ ቃሉም "ስለ ክፉው ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ….." (2ጴጥ.1÷4) ይላል፡፡ መለኮታዊ ባሕርያት የሚባሉት መንፈስ ቅዱስ ዜጋ በሆነው ሰው ውስጥ ባለማቋረጥ የሚያፈራቸው ፍሬዎች ናቸው (ገላ.5÷22) ፡፡

ዜጎች የመንግሥቱን ሕይወት የመኖር ግዴታ አለባቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ዜጎችን በዓለም ላይ ምን አድርጎ እንዳስቀመጣቸው በማያወላዳ ሁኔታ እንዲህ ብሎ ይነግረናል፡፡ "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ "… እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" (ማቴ. 5÷13-16) በማለት፡፡ ይህ ክፍል የዓለምን መሠረታዊ ችግርና የዜጎቹንም ተለዕኮ ይነግረናል፡፡ ዓለም በአልጫነትና በጨለማ የተዋጠች ናት፡፡ ስለዚህም የዜጎቹ ተልዕኮ ዓለምን ለማጣፈት ጨው ጨው ማለት ደግሞም የዓለምንም ጨለማ ለመግፈፍ መልካም ሥራን በመስራት ብርሃናችን እንዲታይ ለሁሉም በሚታይ መልኩ መቀመጥ እንዳለብን ቃሉ ይናገራል፡፡





የመንግሥቱ ዜጎች ኑሯቸው ከዚህ ምድር ካሉ ሰዎች የተለየ ነው፡፡ የኑሯቸው ፍልስፍና ከሰማይ የተገኘ በመሆኑ ዓለምን ግራ ማጋበትና ማስደነቅ አለባቸው፡፡ ይህንን ትምህርት ተመልከቱ (ማቴ.5-7፣ 1ጴጥ.2÷8-17)፡፡ የዓለምን ሥራ ባለመድገም የሚኖሩ ናቸው፡፡ ቃሉም "…በዚህ ነገር ወደዚያ መዳራት ብዛት ከእነርሱ ጋር ስለማትሮጡ እየተሳደቡ ይደነቃሉ…." (1ጴጥ.4÷4) ይላል፡፡ በክርስቶስ የሆነ ሁሉ አዲስ ፍጥረት ስለሆነ (2ቆሮ.5÷17)፡፡ የእግዚአብሔርም ዘር በውስጡ አለ፡፡ ይህም የመንግሥቱ ዘር ነው፡፡ ዘሩ በውስጡ ሲያድግ መንግሥቱም ያድጋል፡፡ የሚያፈራም ከሆነ ለፍጥረት የበኩራት ዓይነት ይሆናል፤ ለእግዚአብሔር ደግሞ ምርጥ ትውልድ፡፡ ያን ግዜ ዓለምንም በእምነቱ መኰነን ይቻላል፤ ይህም የተወለደበት ዓላማ ነውና፡፡ ይህንንም ትልቅ ተልዕኮ መፈጸም የሚቻለው በፅድቅ መርሕ ከተመላለሰ ብቻ እንጂ ከተደባለቀና የጨውነት ጣዕም ወደ አልጫነት ከተለወጠ፤ ወይም ጨው ጨው ማለት ካልቻለ ድንጋይ ተብሎ መጣል ዕድል ፈንታው ይሆናል፡፡ ደግሞም በእርሱ ሕይወት ካልተገለጠና የዚህ ዓለምን የጨለማ ኑሮ መግለጥ ካልቻለ ብርሃን ተብሎ ለተጠራው ሕዝብ ወዮለት!

እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግስት ዜጋ የሆነ ሁሉ ያገኘውን መብት ፣ ኃላፊነትና የኑሮ ግዴታዎች በማወቅ

መመላስ ይኖርበታል፡፡ እኛ ሰማያዊ ዜግነት ያለን በምድር የምንኖር የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን፡፡ ስለዚህ በመንግሥቱ መርሕ በመኖር ለምድራችን የመልካም ነገር ሁሉ ምሳሌ እንሁን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## “መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን”

(ማቴ.6÷9)

5

# የመንግሥቱን ራዕይ መያዝ

በመንግሥቱ የሚኖር ሰው ሰማያዊ አስተሳሰብን የያዘ ነው፡፡ የተለወጠም ሰው የምንለው አስተሳሰቡ ፍፁም ሰማያዊና እግዚአብሔራዊ የሆነውን ነው፡፡ በሰማያዊ አስተሳሰብ በምድር መኖር ስንል ምን ማለታችን ነው? ሰማያዊ አስተሳሰብ ማለት መለኮታዊ የሆነውን ንድፍ (ራዕይ) አግኝቶ በምድር ሰማይን ወይም በመንግሥቱ ውስጥ ያለውን ሕይወት የሚኖር ነው፡፡ ቃሉም "...በቀረላችሁ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ፤" (1ጴጥ.4÷1-2) ይላል፡፡ የራዕይ ሰው መሆን ማለት ደግሞ በሕይወቱ ሊፈጸም ያለውን የእግዚአብሔርን ዓለማና ዕቅድ አውቆ ለዚህም የሚኖር ስብዕና ያለዉ ነው፡፡

የመንግሥቱን ራዕይ የያዘ ሰው በምድር ላይ ሕይወቱን በዘፈቀድ እንዳይመራ የሚያደርግ አጥር የሚሆነው መርሕ አለው፡፡ ቃሉም "ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፤" (ምሳሌ 29÷18) ይላልና፡፡ መረን ልቅ ማለት ነው፡፡ ምንም ራዕይ የሌለው ሰው መረን ነው፡፡ በሕይወቱም የሚያከናውነው ተግባርም የለም፡፡ ስለዚህም እንዲህ ዓይነት ሰው በነፈሰበት የሚነፍስ የኔ የሚለው ነገር የሌለው ነው፡፡ ሰማያዊ ራዕይ





ያለው ሰው ግን ትጉህ ነው፡፡ ባገኘው ራዕይ መሠረት ይሠራልና፡፡ ሕይወቱንም በመንግሥቱ መርህ ይመራል፣ ሥርዐትም (discipline) አለው፡፡

የመንግሥቱ ራዕይ ከሰማይ የሚመጣ ነው፡፡ ሰጪውም የሰማይ አምላክ እንጂ በሰው የአእምሮው ቀመር የሚመጣ ምኞት አይደለም፡፡ የሰማያዊ ራዕይ ጥቅል ሃሳቡ በምንኖርበት ሥፍራ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰፋና መንግሥቱ ሁሉን እንዲገዛ መኖር ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ሁሉ ለእርሱ እንደተገዛለት አናይም ቃሉም፣ "አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም" (ዕብ. 2÷8) ይላልና ፡፡ በመጨረሻው ግን ሁሉም መንግሥታት ለእርሱ እንደሚሆኑና እንደሚገዙ ቃሉ እንዲህ ብሎ ይናገራል፣ "የዓለም መንግሥታት፣ የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ሆነች፤ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" (ራእ.11÷15)፡፡

በእግዚአብሔር የአገዛዝ ዕቅድ ውስጥ ሰው ትልቅ ሥፍራ እንዳለው ከአፈጣጠሩ ጀምሮ መረዳት እንችላለን፡፡ ይኸውም ሰውን ሲፈጥር "ሰውን እንፍጠር" በማለቱ ከሌሎች ፍጥረት ለየት እንዲል አድርጎታል፡፡ እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ ስምን ያወጣላቸው ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው በማለት ቃሉ ይናገራል (ዘፍ.2÷19-20)፡፡ ይህ እንግዲህ ከሰው በስተቀር ስም ይዞ የተፈጠረ ፍጡር

አለመኖሩን ያሳየናል፡፡ በሥላሴ ምክር ግን ሰውን እንፍጠር ብሎ ሰው መፈጠሩ ሰው በእግዚአብሔር ውስጥ የነበረ የዘላለም አሳብ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ከሰው በስተቀር ለሌላው ፍጥረት ያልሰጠውን መልክና ምሳሌ ለሰው መስጠቱና እንዲሁም የፍጥረት ዘውድ አድርጎ ምድርን እንዲያስተዳደር ሥልጣን መስጠቱ ነው፡፡ "እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር... በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ይግዙ" (ዘፍ. 1÷26-28) ይላል፡፡ ነገር ግን ይህ ምድርን የማስተዳደርና ፍጥረትን የመግዛት ስልጣን በሰይጣን በተቀነባበረ ሽንገላ አማካኝነት አዳም አሳልፎ ቢሰጥም በእግዚአብሔር አሳብ ግን ገዥ ሆኖ መኖር ሰውን የወለደበት ዓላማ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ልጁን በመላክ እግዚአብሔር የሆነው እርሱ የሰው ልጅ በመሆን የሰው የሆነውን ስልጣን ያስመለሰው፡፡ እንግዲህ ይኽን ስናይ፣ ገዢ ሆኖ በምድር መመላለስ በመጀመሪያም ሰው የተወለደበት በኋላም ደግሞ በክርስቶስ የተዋጀበት የእግዚአብሔር የጸና ሐሳብ ነው የምንለው፡፡ ሰይጣን የአዳም ልጆች መዋጀት እስኪሆን ለሰው በተሰጠው ሥልጣን ሰውን ቢገዛም አሁን ግን በክርስቶስ ለሆኑት ተገዢ ሆኗል፡፡ እግዚአብሔር የሰው ልጅ ተብሎ የተጠራውን ልጁን ብቻ ሳይሆን ይህንን የምስጋና ዘውድ እንዲጭን ያደረገው ቃሉም "ብዙ ልጆችን ወደ





ክብር ሲያመጣ..." (ዕብ.2÷10) እንደሚል፡፡ የመንፈስ ፍሬ የሆነውን እኛንም ጭምር ነው፤ ወደዚህ የንግስናና የክብር ሕይወት ያመጣን፡፡ ስለዚህም በክርስቶስ የሆኑ ሁሉ ከሞት ፍርሃት ነፃ ወጥተዋል፤ ከሰይጣን የአገዛዝ ቀንበር ተላቀዋል፤ ደግሞም በክርስቶስ ባገኙት የልጅነትን ሥልጣን ሁሉ ይገዛላቸው ዘንድ ተደርጎላቸዋል (ዮሐ.1÷12)፡፡ ይኽንን ገዢነት ግን የምንለማመደው በሰማይ ሳይሆን በምድር ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን አማኞች ከጌታ በተቀበሉት ሥልጣን ይገዛሉ፤ ደግሞም በክርስቶስ በአካል መገለጥ ወይም በዳግም ምጽዓቱ ጊዜ ለአንድ ሺህ ዓመት በምድር ላይ ከእርሱ ጋር በመንገስ ይገዛሉ (ራዕ.20÷4-6)፡፡ ሰማይ ግን የእግዚአብሔር የአገዛዙ ቦታ ነው እንጂ ለሰው የመግዣ ቦታ አይደችም (ራዕ.4÷8)፡፡ በሰማይ እንደ ንጉስ ልጆች (ልዑል) እንኖራለን፣ እንመላለሳለን እርሱንም እናመልካለን፡፡

የመንግሥቱን ራዕይ የያዘ ሰው የእግዚአብሔር አገዛዝ በምድር ሁሉ ላይ በሙላት ትገለጥ ዘንድ በመፈለግ በፊቱ ያገለግላል፡፡ የመንግስቱ ቃል እንደሚል "መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" (ማቴ.6÷9)፡፡ በሰማይ ያለችው የእርሱ ፈቃድ በምድር እንድትሆን በጸሎቱ ይጋደላል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በላይ

በመንግስተ ሰማይ ያለምንም መከልከል ይፈጸማል፤ በዚያም ፈቃዱን የሚፈጽሙ መላዕክትና ቅዱሳን አሉ፡፡ በምድር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰዎችና በፍጥረቱ መሃል በጊዜው ውስጥ እንዳይፈጸምና እዲዘገይ የዚህ ዓለም ገዢ ይቃወማል፤ ያዘገያልም፡፡ (ዳን.10÷12-13)፡፡ የቅዱሳን ተግድሎ (ውጊያ) ሊሆን የሚገባው የእግዚአብሔር ፈቃድ ልክ በሰማይ እንደሚፈጸመው፣ ያለምንም መከልከል በሰው ልጆችና በፍጥረቱ ላይ በምድር እንዲገለጥ በማድረግ ላይ መሆን ይገባል፡፡

በሰማይ ያለው የእርሱ ፈቃድ በምድርም ይፈጸም ዘንድ የሚፈልገው ሃሳቡ የሰዎች መዳን ወይም ከጨለማዉ መንግሥት ወደ ብርሃን መንግሥት መምጣት ነው (1ጢሞ.2÷3-4)፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ለዚህ ፈቃድ መፈጸሚያ ትሆን ዘንድ በዘላለም ምክሩ ወስኗታል፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ጥበባዊ አሰራሮች የሚገለጥባት በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ወሳኝ ሥፍራ ያየዘች ተቋም እንጂ ድርጅት አይደለችም፡፡ ለምን? ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ምሥጢር የተካፈለችና የዕርቅ መልዕክት ስለያዘች ነው (2ቆሮ.5÷18-20)፡፡ ከዚህም ተግባሯ በተጨማሪ፣ ለዚህ ዓለም ገዥ ለሆነው ለሰይጣን ደግሞ በምድር እንዳይሰራ





የምታግድም ዕንቅፋት ናት፡፡ ቃሉም "የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሰራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ" (2ተሰ.2÷7) ይላል፡፡ ቤተ ክርስትያን ከእግዚአብሔር ጋር ባላት ግንኙነት የቤተሰብ ቅርጽ ስትይዝ (ኤፌ.2÷19)፤ ከዚህ ዓለም ገዢ ጋር በምታደርገው ውጊያ ግን የወታደር መልክ ይዛለች (ኤፌ.6÷10-18)፡፡ እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን የማዳን ተልዕኮ በመያዝ ሁሉን ለክርስቶስ ለማድረግ በምድር የምትሰራ ሕያው የሆነች የእግዚአብሔር መሣሪያ ነች፡፡ ቃሉም " በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናል፣ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው" (ኤፌ.1÷9-10) ይላል፡፡

እንግዲህ ምን ያህል ልባችን ለፍቃዱ መምጣትና ለመንግሥቱ መገለጫ ይሆን ዘንድ እንደተዘጋጀ አላውቅም፡፡ ነገር ግን በምድር መንግሥቱ ማለትም አገዛዙ በእኛ አማካኝነት ሊሰፋና ሊገለጥ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

"....በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ።"

(ዮሐ. 16፥33)

# 6

## በመንግሥቱ መኖር

ክርስቲያን በአንድ ጊዜ በሁለት መንግሥት ውስጥ ይኖራል፡፡ ይህም በእግዚአብሔር መንግሥትና በሰው መንግሥት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም አማኞች ሁለት ዜግነት አላቸው፤ በሥጋ እንደ መወለዳቸው የሚያገኙት ምድራዊ ዜግነትና በመንፈስ በመወለዳቸው ደግሞ ሰማያዊ የሆነ ዜግነት ይቀበላሉ፡፡ በምድር ዜጋ በሆኑበት ከሰው መንግሥት በስተጀርባ የሚሰራ የጨለማ ዓለቃ አለ፡፡ ለምን ዓለማዊ መንግሥት ስለሆነ፡፡ ደግሞም ከእግዚአብሔር በመወለዳቸው መንፈስ ቅዱስ በሚሰራበት መንግሥት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣቸው ጥበብ በመኖርና በመመራት በዓለም ላይ የጽድቅ ተጽዕኖ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ዓለም የሚለው ቃል በሦስት ዐበይት ክፍሎች ተከፍሎ እንገኛለን፡፡ ይኸም፡ በመጀመሪያ ግዕዙን ዓለም ምድርን (የሐሥ. 17÷24፣ ማቴ. 13÷35) ፡፡ ሁለተኛው የዓለም ነዋሪ ሰዎችን (ዮሐ.3÷16፣ 1÷10፣ 17÷21) ፡፡ በሦስተኛ ዓለማዊነትን (operating system) ያመለክታል (1ዮሐ.2÷15 ፣ ማቴ.16÷26 ፣ 1ቆሮ.7÷31 ፡፡

በቅደም ተከተል እንዳየነው የመጀመሪያውና ሁለተኛው የዓለም ትርጓሜ በራሱ ኀጢአት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ሦስተኛው ዓለም የሚለው የግሪኩ ቃል "ኮስሞስ" ይለዋል ለዓለማዊ ጉዳዮች ማለትም ምድራዊ ሽቀጣ ሸቀጦች፣ ሀብት፣ ፈንጠዝያ፣ ውስጡ ባዶ ሆኖ የሚያማልል፣ ምኞትንም በማነሳሳት ከእግዚአብሔር እንድንርቅ የሚያባብለንና ለተሰጠ ክርስቲያነዊ ሕይወት መሰናክል የሚሆኑ ነገሮችን የሚያካትት ትርጉም ይዟል፡፡ ይህ እንግዲህ እግዚአብሔርን የሚቃወም ሥርዓት እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

ዓለም (ዓለማዊነት) ሰይጣን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚገዛበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም እንግዲህ ከሚታየው ነገር በስተጀርባ በመንፈሳዊው ዓለም፣ እግዚአብሔርንና መንግሥቱን ለመቋወም የታቀደና የተቀናጀ ሥርዓት እንዳለ ያሳየናል፡፡

እንግዲህ ይህ ዓለም ቃሉ እንደሚነግረን "ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን" (1ዮሐ.5÷19) እንደሚል፡፡ ይኸ ዓለም በክፉ የተያዘ ነው፡፡ ደግሞም የተዋቀረበት ሥርዓት ዓለማዊ ነው፡፡ ዓለምንም የሚያስተዳድረው ሰይጣን ነው፡፡ ቃሉም "የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" ይላል (2ቆሮ. 4÷4)፡፡ ሰይጣን የሰዎችን ልብ አሳውሮ በዚህ ዓለም





ሥርዓት ውስጥ ከቶ ይገዛል "..የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፡" (ዮሐ. 14÷30) ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከዚህ ዓለም ሊያድነን ሞተ (ገላ.1÷4)፡፡

እንግዲህ ሁለት መንፈሳዊ መንግሥቶች እንዳሉ ቃሉ ይናገራል፡፡ ይኸም የጨለማው መንግሥት (ሰይጣን የሚያስተዳድረው) እና ሁለተኛው የብርሃን መንግሥት (እግዚአብሔር የሚያስተዳደረው) በመባል ይጠራሉ፡፡ ሰዎች ሁሉ ከፊተኛው አዳም ስለተገኙ ከፋው ከሚገዛው ዓለም ጋር የተሳሰሩና የተገናኙ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ በማመን ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱ አዲስ ፍጥረት ስለሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት በሚሰራበት ክልል ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ታዲያ እንዴት ከጨለመው መንግሥት ወጥተን ወደ ብርሃን መንግሥት እንሸጋገራለን? እንዴትስ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እንኖራለን? ካልን ዳግመኛ በመወለድ እንደሆነ ቃሉ በማያሻማ መልኩ ይናገራል (1ጴጥ.1÷3 ዮሐ.3÷6) ፡፡ መንግሥቱ ውስጥ ለመኖር ሁል ጊዜ በመንፈስ የሰውነትን ሥራ እየገደልንና በመንፈስ ቅዱስ በመሞላትና በመንፈስም መመላለስ ያስፈልጋል (ሮሜ 8÷13፣ ገላ.5÷16) ፡፡

እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ለኀጢአት መሞት ከዓለም ጋር የነበረ ግንኙነት ማብቂያ ሲሆን ትንሳኤው ደግሞ ወደ

መንግሥቱ መግቢያና ከእርሱ ጋር ሕያው የሆነ ሕብረት ማምጫ (መጀመሪያ) ነው (1ጴጥ. 1÷3-5፡፡ ስለዚህ ከክርስቶስ ሥራ ጋር በመተባበራችን ምክንያት ባገኘነው ክቡር የሆነ እምነት የተነሳ እግዚአብሔር የት እንዳደረሰን አይታችኋል? እንግዲህ ከዚህ በመነሳት በመንግሥቱ ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለብን መንፈስ የሚያስተምረንን ለማወቅ ልባችን ሊሰፋ ይገባል፡፡ ለዚህም ተደላድለን ከተቀመጥንበት ሥፍራ መነሳት በተባለልን ልክ ለመሆንና ለመኖር እንዘጋጅ፡፡

እግዚአብሔር እንድንኖረው በክርስቶስ ያቀደው ሕይወት ምን ዓይነት ነው? ቆይ ላፍታ ቆም እንበል! ለመሆኑ ክርስቶስንስ ምን እንዲሆንልን ሰጠን? ወደ መጽሐፉ ከልባችን እንጠጋ፤ ቃሉም የሚለውን እንስማ፤ "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፤ ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያ ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ" (ቆላ.3÷1-4) ይላል፡፡

እግዚአብሔር ክርስቶስን ለጉደለታችን መሙያ አድርጎ ሳይሆን የሰጠን ሕይወት እንዲሆንልና እንዲበዛልን ሰጥቶናል፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ





የሠራውን ሥራ እንዲያው በጸጋው የእኛ ስራ አድርጎ በመቁጠር ከርሱ ጋር ተባባሪዎች እንደሆንን አድርጎ ያስቀምጠናል እንዲህ በማለት፡-

- ከክርስቶስ ጋር ሞተናል፤ (ቁ.3)
- ከክርስቶስ ጋር ተነስተናል፤(ቁ.1)
- ከክርስቶስ ጋር ተሠውረናል፤ (ቁ.3)
- ከክርስቶስ ጋር እንገለጣለን )ቁ.4)
- አሮጌውን ሰው አውልቀን (ቁ.9)
- አዲሱን ሰው ለብሰናል (ቁ10)

<u>ከክርስቶስ ጋር ሞተናል</u>፤ እኛም እንደ ሞትን ወይም ከሞቱም ጋር እንደተባበርን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ሮሜ 6÷3-11)፡፡ የእርሱ ሞት ለኃጢአት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ፤ የእኛም ሞት ለኃጢአት ነዉ፡፡ ከዚህም አንፃር የኃጢአት ሃይል ጉልበት አግኝቶ ሊቆጣጠረን አይችልም፡፡ ለምን? ኀጢያት እንዳይገዛን ኀጢያት ለሚያስታውቀውና ለሚየነሳሳው ሕግ ሞተናል "በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኀጢያት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሰራ ነበርና፤ አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ለሞትን ከሕግ ተፈተናል ስለዚህም በአዲስ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም" (ሮሜ 7÷5-6)፡፡ ሥጋ የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞችን ይዟል፡፡ የመጀመሪያው ሥጋ አካልን ወይም ሰውነታችን ሲያመለክት

ሁለተኛው ኀጢያተኛው ባህሪ ወይም አሮጌውን ሰው ያመለክታል፡፡ እንግዲህ በብልቶቻችን ይሰራ የነበረው ይህ ኀጢያተኛ ተፈጥሮ ነበር፡፡ አሁን ግን አስሮን ለነበረው ስለ ሞትን ከሕግ እስራት ነጻ ወጥተናል፡፡ አሁን በአዲሱ የመንፈስ መመሪያ ነጻነትን አግኝተን እንኖራለን፡፡ በክርስቶስ ያላመኑ በኀጢያተኛ ባሕሪ ቁጥጥር ውስጥ ናቸው፡፡ አማኞች ግን ከኀጢያት ባሕሪ ነጻ ወጥተዋል (ሮሜ 8÷9)፡፡

በክርስቶስ የዳነ ሁሉ ከኀጢአት ኃይል ድኗል ምክንያቱም ኀጢያትን ለሚያነሳሳው ሕግ ሞተዋልና፡፡ ኀጢያት አሁን በዓለም ውስጥ እየሰራ፤ ነገር ግን ከክርስቶስ ሞት ጋር የተባበሩ አማኞች ሁሉ የኃጢያት ኃይል ስለማይሰራባቸው ተገደው የሚሠሩት ወይም የሚፈጽሙት ኃጢያት አይኖርም፡፡ ቃሉም "በኃጢአት የሞትን እኛ ለወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ(በኃጢአት) እንኖራለን" ሮሜ 6.2 ይላልና፡፡

<u>ከክርስቶስ ጋር ተነስተናል</u>፤ ከሞቱ ጋር ከተባበርን ከትንሳኤው ጋር መተባበራችን የማይቀር እውነት ነው፡፡ ከሞት ከተነሳን በኃላ አዲስ ሕይወት ተቀብለናል፡፡ ይህ ሕይወት ቃሉ እንደሚል አዲስ ነው እንጂ ካለፈው ሕይወት የሚቀጥል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሰራው





አሮጌውን የማደስና የመጠገን ሳይሆን ፤ አዲስ ሰውን የመፍጠር ነው፡፡ ይህ አዲስ ሕይወት ወደፊት የምንደርስበት ግብ ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ የተፈፀመና የሚፈጸም እውነት ነው፡፡

ስለዚህ የተነሳነው የክርስቶስ ሕይወት በእኛ ተገልጦ ዓለምን በኑራችን እንድንኰንን ነው፡፡ "በእምነቱ ዓለምን ኰነነ" (ዕብ.11÷7) ፡፡

<u>ከክርስቶስ ጋር ተሠውረናል</u>፤ ይህ ቃል በክርስቶስ ውስጥ መሆንን እና መኖርን የሚያመልክት ነው፡፡ እንግዲያውስ ማን ሊያገኝን፤ ማን ከእርሱ ሊነጥለን ይችላል? አንድ ጊዜ አንዲት ክርስቲያን እህት እንዲህ እያለች ትዘምራለች "በእጁ መሀል ስላለሁ ምንም አልሆንም" የሚል ዜማ ስትቀኝ አጠገቧ ይሰማት የነበረው ሰው ትክሻዋን መታ መታ በማድረግ "ብዙም ሳትኩራሪ ምናልባትም በጣቶቹ መካከል ሾልከሽ እንዳትወድቂ ተጠንቀቂ" ሲላት በዚህ ጊዜ እንዲህ መለሰችለት "በዚህስ አትስጋ እኔ እራሱ ከጣቶቹ መካከል አንዱ ነኝ አለችው" አዎ በድነት ጊዜ የገባነው ወደ ክርስቶስ አካል ነው፡፡ ስለዚህ የእርሱ ብልቶች ነን፤ በእርሱ ውስጥ አለን፡፡ ቃሉም እንደሚል "...እንግዲህ እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካል ብልቶች ናችሁ::" (1ቆሮ. 12÷27)፡፡

<u>ከክርስቶስ ጋር እንገለጣለን፤</u> ይህ በዳግም ምጽዓት ጊዜ የሚሆንን ክስተት አመልካች ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን በአባቱም ቀኝ በክብር ተቀምጧል (ሮሜ.8÷34)፡፡ ይህም የሰው ልጅን ወክሎ በሰማይ መቀመጡን ያሳያል፡፡ "እነሆ ሰማያት ተከፍተው፣ የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ፡፡" (ሐሥ. 7÷56) ይላል፡፡ በዘላለም የመጠሪያ ስሙ "ቃል" የሆነው እርሱ (በዮሐ 1÷1) ከአባቱ እቅፍ ወጥቶ (ዮሐ1÷18) ወደ አባቱ ቀኝ ለመሄድ ምንም እንኳን መንገዱ አጭር ቢሆንም እርሱ ግን ረጅሙን መንገድ መረጠ፡፡ ለምን ብለን ከጠየቅን ከእኛ ጋር አብሮ ለመቀመጥ ስለፈለገ ነው፡፡ አሁን በሰማይ "የሰው ልጅ" የተባለው የእግዚአብሔር ልጅ ከእርሱ ጋር በመንፈስ እንደ ተሠወርን በመጨረሻም ቀን ከእርሱ ጋር በክብር እንገለጣለን፡፡ አቤት የመለኮት ሃሳብ! አሁን በክርስቶስ ከብረናል፤ ይህ ክብር ግን ለዓለም ገና አልተገለጠም፡፡ ቃሉም እንደሚል "ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን ስላላወቀው ነው፡፡ ወዳጆች ሆይ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም" (1ዮሐ. 3÷2) ይላል፡፡ በክርስቶስ የሆነውንና ያገኘነውን ማንነት ዓለም ልታውቀው አትችልም፡፡ ለምን ከዓለም ተሰወረ? ይህን ምስጥር በዚሁ ቃል ታገኛላችሁና ተደንቁ መንፈስ ቃሉን እንደ ገለጠልኝ መጠን እጽፋለሁ፡፡





በክርስቶስ ያገኘነውን የማንነታችን ክብደት ምን ያህል መሆኑን ለማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈልጓል፡፡ በዓለም ያሉት እግዚአብሔርን ማወቅ ባልወደዱ መጠን እኛንም አያውቁንም፡፡ ደግሞም አይቀበሉንም ስለዚህም ለዓለም ምስጥር የሆነው ዓለም እግዚአብሔር ማወቅ ባለመውደዷ ነው፡፡

የሰው ልጅ የተባለው ክርስቶስ እኛን የእግዚአብሔር ልጆች ሊያደርገን መጣ "ቃልም ሥጋ ሆነ" ዮሐ.1÷14 በማለት አምላክ ሰው መሆኑን ያሳያል፡፡ እንግዲህ የማይሞተው በሚሞተዉ ሰው በመምጣቱ ወደ ሰው ዘር በመግባት ከሰው ልጆች የዘር ሐረግ ጋር አብሮ ተቆጥሯል፤ መለኮት ከሰው ልጆች ጋር ተዛምዷል፡፡ በትንሳኤው ደግሞ የሰው ልጆችን ወደ መለኮት ዘር አስገብቷል፡፡ ከዚህ ካገኘነውና ከተካፈልነው ሕይወት የተነሳ ከእርሱ ጋር በክብር እንድንቀመጥ ብቻ ሳይሆን ከእርሱም ጋር በክብሩ እንድንገለጥ አስችሎናል፡፡ ክብሩም ሙሉ በሙሉ ለዓለም የሚታየው በሁለተኛ መመለስ ጊዜ እንደሆነ ቃሉ ይናገራል (ሮሜ 8÷17-25)፡፡

<u>አሮጌውን ሰው አውልቀን፤</u> ይኸ ማወለቅ የሚለው ሐሳብ ያደፈን የቆሸሸን ልብስ በማውለቅ አዲስን ልብስ እንደ መልበስ ነው፡፡ በክርስትቲያን ሕይወት ሁለት ማንነቶች

መንግሥት ነውና በማስተዋል እንሂድ፤ ትምህርታችንም አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፈን እንድጥል የሚያደርግ ይሁን::

<u>አዲሱን ሰው ለብሰናል፤</u> ይኸ እንግዲህ በወደ ፊት ጊዜ እንደሚሆን የቀረበ ሳይሆን፤ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የሚፈጸም እውነት ነው:: አዲሱን ለመልበስ የግዴታ አሮጌውን ማውለቅ አለብን:: "...አሮጌውን ሰው አስወግዱ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ በእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ::" (ኤፌ.4÷23-24) ይላልና:: በአሮጌው ላይ አዲስ መልበስ ወይም መደረት አንችልም:: ስለዚህም አስወግዱት በማለት ሐዋሪያው ያሳስባል:: አሮጌውን ማስወገድ ከቻልን አዲስ መልበስ ይገባናል:: ይህም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረና በሕይወት መንፈስ ሕግ የሚመራ አዲሱን መንፈሳዊ ሰውነት መልበስ ይኖርብናል:: ይህ ልብስ እንደ መለዮ የእርሱ የሆኑት ብቻ የሚለብሱት ልብስ (መንፈሳዊ ኑሮ) ነው:: ይሄ ልብስ በሌላ ክፍል ላይ "....ክርስቶስን ለብሳችኋልና::" (ገላ.3÷27) በማለት ይናገራል:: የክርስቶስ ጸባይ በውስጣችን ጎልቶ ካልወጣ ማንም የክርስቶስ ናችሁ ማለት አይችልም::





የአዲሱን ሰው ኑሮ ለመኖር የታደሰና የተለወጠ አእምሮ ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር ቃል የአእምሮ መታደስን ልንይዝ እንደሚገባን ያስተምረናል ይኸውም፡- "...በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ12÷2) ይላል:: በክርስትና ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የምንችለው በአእምሮአችን ስንታደስና ዓለምን ሳንመስል ከኖርን ነው:: በዋናነት ክፍሉ ዓለምን አትምሰሉ ሲል በዓለም ፍልስፍናና አስተሳሰብ አትያዙ ማለት መሆኑን መረዳት አለብን፤ ክፍሉ የሚያወራው ስለ ሃሳብ ስለሆነ:: ያልታደሰ አእምሮ የሚያስበው ስለ አሮጌው ሰው ሥራ ነው:: የታደሰው ግን የአዲሱን ሰው አካሔድ ብቻ ስለሆነ በመታደስ ተለወጡ ይላል::

እንግዲህ በአዲሱ ሰው ፤አዲስ ሐሳብ፣ አዲስ የሕይወት መርህና አዲስ ምግባርን ማሳየት ይኖርብናል:: መሻታችንም ሰማያዊው ነገር ላይ መሆን አለበት:: ቃሉም እንዲህ ይላልና "እንግዲህ... በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤" (ቆላ. 3÷1):: ለመሆኑ በላይ ያሉ ነገሮች ምንድ ናቸው? ደግሞም ሐዋርያው መልሶ "አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን"(ቆላ.3÷2) ይላል:: ትኩረታችሁ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን ሲልስ? እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ የሆነ መልስ ሊያገኙ ያስፈልጋቸዋል::

# ምዕራፍ ሰባት

“ ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ የእግዚአብሔር መንግስት ወደ እናንተ መጥታለች።”

(ማቴ. 12፥28)

## 7

## በመንግሥቱ ውስጥ የሚሠራ መንፈስ

መንፈስ ቅዱስ ማነው? መንፈስ ቅዱስ ራሱ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመለኮት አንድ ነው፡፡ ሆኖም በአካል፣ በስምና በግብር ሦስት ነው፡፡ ይኸውም በሰማይ አብ፣ ሰው ሆኖ ወደ ምድር የመጣው ወልድ፣ ዳግም በተወለዱ አማኞች ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

እግዚአብሔር አብ የሁሉ ነገር ደራሲ ወይም የሚታየውና የማይታዩትን ፍጥረታት የጸነሰ የዘላለም ዕቅድ ባለቤት ነው፡፡ እግዚአብሔር ወልድ አዳኛችን በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ የነበረውን የሰራና የፈጠረ ነው፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለፍጥረት ውበትን የሰጠና የክርስቶስን ሥራ በግለሰብ ደረጃ እንድንረዳ የሚያደርግና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ ነው (ገላ. 4÷4፣ ሮሜ 8÷28-30፣ ማቴ. 24÷36፣ ዮሐ. 1÷1-3፣ ቆላ. 1÷15-17፣ ዮሐ. 5÷21፣ ዮሐ. 16÷8፣ ቲቶ 3÷5)፡፡

መንፈስ ቅዱስ በሁለቱም ኪዳን መካከል ይሰራ የነበረ የሥላሴ አካል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን መሲሁን በሚያመለክቱ ጥላዎች አማካይነት ሲመጣ፤ በአዲስ ኪዳን ግን በራሱ በክርስቶስ አማካይነት መጥቷል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ጀምሮ እስከ ትንሳኤው ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ሃይል ይሰራ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ አገልግሎቱን ሲጀምር በተለየ መንገድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ እንደነበር የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ብሎ ይናገራል፡-

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌል እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትን ነፃ እወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል" (ሉቃ. 4፥17-18)፡፡

በሥላሴ ሥራ ውስጥ አብ ቀቢ፣ ወልድ ተቀቢ፣መንፈስ ቅዱስ ቅባት ሆኖ ተገልጧል፡፡ ክርስቶስ የሚለው ስም በራሱ ትርጓሜው የተቀባ ማለት ሲሆን ይህም በማን? እና በምን? የሚል ጥያቄ ቢነሳ የተቀባው በአብ፤ በምን ለሚለው ደግም በመንፈስ ቅዱስ ፤ ማለት እንችላለን፡፡

የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በመሲሁ ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመግለጥ እንደነበረ በጊዜው የነበሩት ፈሪሳዊያን (የሃይማኖት አባቶች) አልገባቸውምና መንግሥቱን ያመጣውን ንጉስ ሲገፉት እናያለን፡፡ ለመሆኑ ይጠብቁት የነበረው አመላክ-መር መንግሥት ምን ዓይነት ይሆን? ዓለምን በጊዜው ከሚያስተዳድሩት በገዛ ምድራቸው እየጨቆኑ ከሚያስተዳድራቸው ከሮማዊያን ቅኝ አገዛዝ ነፃ





የሚያወጣ ሥጋዊ (ቁሳዊ ) ጦር የሚጠቀም መሪ (ንጉስ) ነበር የሚፈልጉት፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ገጽታዋ መንፈሳዊ የሆነችና መንፈስ ቅዱስ በዋናነት የሚሰራበት አገዛዝ ናት፡፡ በዚህም መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ከተገዙበት አጋንንታዊ አሰራርና ከኃጢያት ባርነት ነጻ በማውጣት የመንግሥቱ ዜጋ በማድረግ መንግሥቱን ያሰፋል፡፡

ሰይጣን ለብዙ ሺህ ዓመታት ብቸኛ የዚህ ዓለም ገዥ ነበር፡፡ ነገር ግን በወንጌል አገልግሎት ድል ሲነሳና ሌላ ተቀናቃኝ መንግሥት በስፍራው መምጣቱን ሲታዩ የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችሁ መኖሩን ማወቅ ይቻላል፡፡ አጋንንትን ማስወጣት ማለት ከሰዎች ልብ የከፉን መንግሥት በማፍረስ ከሰይጣን አገዛዝ ነፃ ማውጣት ነው፡፡ እነዚህን ነጻ የወጡ ሰዎች በልባቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት መትከልና በመንግሥቱ አገዛዝ ማስገባት የመንግሥቱ አገልጋዮች ዋና ተግባር ነው፡፡

በድነት (ደህንነት) ጊዜ ማለትም በዳግም ውልደት የምንቀበለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ቃሉም "...ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ..." (ዮሐ. 7፥37-39) ይላል፡፡ ክርስቶስ ደግሞ በውስጣችን የሚያኖረው የክብር ተስፋውን ነው፡፡ ለዚህም ነው መንፈስ ቅዱስን

የተቀበሉ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግመኛ መመለስ በመጠበቅ ዕለት ዕለት በትጋትና በቅድስና የሚጠብቁት (1ተሰ. 4÷13-18)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ወራቱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እያለ አማኑኤል ሆኖ ከእነርሱ ጋር ነበር እንጂ በእነርሱ ውስጥ አልነበረም (ማቴ.1÷22-23)። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ከመጣ በኋላ እግዚአብሔር የሆነው እርሱ ከእኛ ጋር ብቻ ሳይሆን በእኛ ውስጥም ሆኗል (ዮሐ 14÷15-17)። ይኸም እውነት ለዓለም ምስጥር ነው። ለምን? ዓለም በስሜት ህዋሳቷ በመጠቀም በማየት በመዳሰስ..... ወዘተ ካላረጋገጠች አንድ ነገር አትቀበልም። ደግሞም የለም ትላለች። በክርስቶስ የሆኑት ግን የመንፈስ ቅዱስ መኖር በውስጣቸው እንዳለ በእምነት ስለሚረዱት መንግስቱም በመካከላችን መኖሩን ይመሰክራሉ። እስኪ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን ሥራ በጥቂቱ እንይ፦

## 7.1 መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ድነት የለም፤

"....ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም።" (ዮሐ. 3÷5)።

ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዳግመኛ በመንፈስ ቅዱስ መወለድ እንደሚያስፈልግ ጌታ ኢየሱስ





ክርስቶስ ተናግሯል። እስኪ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እናንሳ እንዴት ወደዚህ ዓለም ልንገባ ቻልን? መቼም መልሱ ለብዙዎች አስቸጋሪ አይደለም፤ የተለየ ዕውቀትንም አይጠይቅም፤ የምንለውስ እንደዚህ አይደል? በመወለድ ነው። እንግዲህ ወደዚህ ዓለም የተቀላቀል ነው በዚህ መንገድ ከሆነ፤ ወደ እግዚአብሔርም መንግሥት የምንገባውና የምንቀላቀለው ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ዳግም በመወለድ ብቻ ነው፡ይህም ውልደት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚፈጸም ነው። ዳግም መወለድ ማለት ሰማያዊ ዜግነትን ማግኘትና ወደ መንፈሳዊም ዓለም በመቀላቀል በአንድ ጊዜ በሁለቱ መንግሥት (dual citizenship) ውስጥ መኖር ማለት ነው።

"...የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም" (ሮሜ. 8÷9)

መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል በቀጥታ ዘራችንና ወገናችንን እንለያለን። የክርስቶስ መንፈስ የእግዚአብሔር ወገን ያደርገናል። መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበለ ድነትን አላገኘም፤ የክርስቶስም ወገን አይደለም፤ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ልጅም ተብሎ ሊጠራ አይገባውም።

## 7.2 መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ቅድስና የለም፤

"..... እብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለመረጡት..." (1ጴጥ. 1÷1-2)።

ቅድስና ሰው ከፉና ርኩስ ከሆነው ነገር ተለይቶ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር ማለት ነው። የተቀደሰ ሰው የሚባለው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የተዛመደ በኑሮ ሁሉ የጠራውን እግዚአብሔርን ለማክበር የቆመ ነው።

ቅድስናን በሰው ልብ ውስጥ የሚተክለው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ትምህርት የአማኞች ቅድስና ክርስቶስ እንደሆነ ይናገራል (1ቆሮ.1÷30-31)። እግዚአብሔር ቅዱሳን ሲለን በእርሱ ቆጥሮን ነው። ቅድስና ሁለት ይዘት ይኖረዋል፦

7.2.1 አሮጌውን ሰው ማስወገድ፤ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ያለው፤ አሮጌው ሰው በክርስቶስ መስቀል ዕለት ዕለት ይወገዳል (ገላ. 5÷24፣ ሮሜ 6÷6)። በቅድስና ውስጥ አሮጌው ሰው አይለወጥም ወይም አይታደስም፣ ይልቁንም የእርሱን ሥራ ገፈን፤ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን፣ አዲስ ሰው መቀበል ነው።

7.2.2 አዲሱ ሰው መታደስ፤ ይህ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ዕውቀትን በማግኘት የሚታደስ ማንነት ነው (ኤፌ. 4÷24)።





መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ቅዱስ ሕዝብ የመፍጠርን ሥራ ባለማቋረጥ ይሰራል።

## 7.3. ያለመንፈስ ቅዱስ ትንሳኤ የለም፤

"ነገር ግን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈስ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወት ይሰጣችል (ሮሜ 8÷11)።

መንፈስ ቅዱስ በዋናነት ሕይወት የመስጠት ሥራ እንደሚሰራ ገና በሰው ፍጥረት ጅማሬ ላይ እናያለን። በዕብራይስጥ ቋንቋ "እፍ" አለ የሚለው ቃልና መንፈስ የሚለው ቃል አንድ ዓይነት ትርጓሜ አለው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር እፍ ብሎበታል፤ የመጀመሪያዉ እፍታ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍ. 2÷7) ይላል። ሁለተኛው እፍታ ከትንሳኤው በኋላ ታይቷል "ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" (ዮሐ.20÷2) ይላል። የመጀመሪያው እፍታ ለሰው አካልን ሕይወት ያስገኘ ሲሆን፤ ሁለተኛው እፍታ ግን ሙት ለሆነው ለሰው መንፈስ የትንሳኤንውን መንፈስ መቀበሉን የሳያል። ግን በሁለቱም እፍታ ጊዜ ሰው የሚቀበለው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሕይወትን ነው። ይህ እንግዲህ

የሚያሳየን መንፈስ ቅዱስ የሕይወት መንፈስ መሆኑን ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሞት ጊዜ ትንሳኤን ያስገኘና የሞትን ጣር ያጠፋ ነው (ሐሥ. 2÷24)፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ካለ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል የሚለው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የትንሳኤ መንፈስ ስለሆነ ነው፡፡

### 7.4. መንፈስ ቅዱስ የርስት መያዣ ነው፤

"እርሱም የርስታችን መያዣ ነው ለእግዚአብሔር ያለውን እስኪያውጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል፡፡" (ኤፌ. 1÷14)

መያዣ(ቀብድ) ሙሉው ወደፊት እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ ለጊዜው በከፊል የሚሠጥ ነው፡፡ በአሁን ጊዜ በከፊል የሚሰጠው ግን የሙሉው አካል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የምንገባበት መንግሥት ምን እንደሚመስል እንድናውቀውና አሁን በከፊል እንድንረዳ በውስጣችን የገባ መንግሥቱን የሚያስተዋውቅ መንፈስ ነው ። የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር፣ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሙሉ በሙሉ እንደሚፈጽምልን የሚያረጋግጥልን መያዣ ነው (2ቆሮ. 1÷22)፡፡ ደግሞ ክርስቶስ ሲመጣ መንፈሳዊ አካልን እንደምንለብስ በውስጣችን ያለው መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ መያዣ ነው (2ቆሮ. 5÷5)፡፡ በተጨማሪም





የእግዚአብሔር ንብረት የሆኑት ሰዎች ሙሉ መዳን ወደ ፊት እስኪመጣ ድረስ ለውርሳችን ዋስትና የሚሰጥ መያዣ ነው (ኤፌ. 1÷14)፡፡ እንግዲህ በእምነት ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ የገባን መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላችን የተነሳ በሰማይ የቀረልን ርስት ወደ ፊት እንደምንወርሰው መንፈስ ቅዱስ ዋስትናችን (መያዣ) ነው፡፡

### 7.5. መንፈስ ቅዱስ እንደማህተም ይሰራል፤

"……በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ ታትማችሁ …." (ኤፌ. 1÷13)

ማህተም የባለቤትነት ማረጋገጫ ማሳያ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የርስታችን መያዣ ብቻ ሳይሆን ርስቱንም እግዚአብሔር ያዘጋጀው ለኛ መሆኑን፣ ያንንም መውረስ እንደምንችል የሚያረጋግጥ፣ በውስጣችን የሚመሰክርልንና በምድርም እያለን እንደ ቅምሻ መንግሥቱን የምናጣጥምበት ነው፡፡ ይህም የዳነ ሰው ሁሉ የክርስቶስ መሆኑና በእርሱ መመረጡን ማረጋገጫ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል ለእግዚአብሔር ተለይተዋል፤ የርሱ ንብረት ሆነው በእርሱ ምልክት ታውቀዋል፡፡

"ስቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑት፡፡" (ኤፌ. 4÷30)፡፡

## 7.6. መንፈስ ቅዱስ የመቃተት ሥራ ይሠራል፤

"…. ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል" (ሮሜ 8÷26)፡፡

በዚህ በሮሜ 8 ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ጊዜ በመደጋገም መቃተት የሚል ቃል ተገልጾ እንመለከታለን ይኸውም፡-

የመጀመሪያው የፍጥረት መቃተት ሲሆን በመንግስቱ ቃል እንደ ተጻፈው "ፍጥረት….ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና" (ሮሜ 8÷22) እንደሚል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቷ፤ በጥፋት ባርነት ውስጥም ይገኛል፡፡ ስለዚህም ከዚህ ባርነት ነፃ ወጥቶ የእግዚአብሔርን ልጆች ክብር መገለጥ ይናፍቃሉ፡፡ የፍጥረት ናፍቆት በእግዚአብሔር ልጆች በክብር መገለጥ የሚመጣለቸውን መታደስ ከሰው ይለቅ ፍጥረት ማወቁ አይስገረምም፡፡ እንግዲህ ፍጥረት ያለምክንያት አልቃተተም፤ አልናፈቀም፡፡ ይኸውም በሰው ውድቀት ምድር እንደተረገመች ቃሉ ይናገራል፤ እንዲህ በማለት "አዳምንም አለው…. ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን ……" (ዘፍ.3÷17)፡፡ ስለዚህም በአዳም ያለመታዘዝ ምክንያት





ምድር ከተረገመች፤ የሰው ልጅ በእምነት ወደ ሆነው መታዘዝ ደርሶ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ክብር ቢደርስ የፍጥረት መታደስ እንደሚሆን ፍጥረት ስለሚያውቅ በመቃተትና በምጥ ውስጥ አለ ማለት እንችላለን፡፡

የእግዚአብሔር ልጆች ርስታቸውን ሙሉ በሙሉ ሲወርሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚታደስበት አዲስ ሰማይና ምድር ይኖራል (2ቆሮ. 5÷17፤ ገላ.6÷15፤ ራእ.21÷1-5)፡፡

ሁለተኛው የእግዚአብሔር ልጆች መቃተት ነው፡፡ "…የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃተታለን" (ሮሜ 8÷23) ይላል፡፡ አዳም ሄዋን በውድቀታቸው ጊዜ ገላቸውን የሸፈኑት ቅጠል ሰፍቶ ለራሳቸው ግልድም በማድረግ ነበር (ዘፍ. 3÷7)፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ቁርበትን በማልበስ የምትክነትን ሥራና ዘመኑ ሲደርስ የሚፈጸመውን የሰው ድነትን ሊያሳይ እንደሚችል፤ ልባቸው የሰፋ የመንግሥቱ ልጆች ይረዱታል (ዘፍ.3÷21፡፡ ቁሩበትንም ለአዳምና ለሚስቱ ለማልበስ በኤደን ገነት ደም ፈሷል፡፡ ይህ እንግዲህ የሰው ቤዛነት በእግዚአብሔር ብቻ እንደሚሆን የሚያሳይና የሰውነቱ (አካሉ) ወደ ነበረበት ክብር መመለሱ የማይቀር መሆኑን የሚያመለክትም መንፈሳዊ ሥርዓት ነው፡፡

የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ስናምን የሚሆነው እንግዲህ የመንግሥት ለውጥ ነው። የመንግሥት ለውጥ ማድረግ ደግሞ ቀላል ነገር አይደለም። በዚህ ዓለም ሥርዓት እንኳን አንድ ሰው ሃገሩን ሲለውጥ የትውልድ ሃገሩን እንዲክድና በለወጠው ሃገር ሕግ ለመመራት ቃለ ማህላ ይፈጽማል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚያ ሃገር ሕግ መሰረት ይኖራል፤ ይተዳደራል፤ ይዳኛልም። በመንፈሳዊውም መልኩ የሚሆነው ልክ እንደዚሁ ነው። ይኸውም የጨለማው መንግሥት አገዛዝ እንዳለ፤ በክርስቶስ የሆኑት ይህን የጨለማ መንግስት ክደው ወደ ብርሃን መንግሥት እግዚአብሔር ወደሚያስተዳድረውና ወደሚገዛበት በመግባት መንግስትና ንጉስ ይቀይራሉ። እንግዲህ ጌታን መከተል በዚህ ዓይነት መንገድ የሚከናወን ነው።

# ምዕራፍ ስምንት

“ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርስዋ በሐይል ይገቡባታል፡”

(ሉቃ 16፡16)

መጥምቁ ዮሐንስ ቀርባለች ብሎ ያወጀላትና ጌታ ኢየሱስ ደግሞ በመካከላችሁ ናት ብሎ የተናገረላት መንግስት አሁንም በዚህ ዘመን ያልተለወጠ የእግዚአብሔርን ሃሳብ የያዘ ስብከት ነው፡፡

መንግሥቱ በታላቅ ድፍረትና በስልጣን ሲሰበክ ሁሉም ሰው ወደዚያ በኃይልና በግፊያ ይገቡባታል፡፡ ቃሉ እንደሚናገር የእግዚአብሔር መንግሥት ከተሰበከ ሰዎች በሽሚያ ይገባሉ ይላል (ሉቃ.16÷16)፡፡ ጥያቄው ግን አሁን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በእንዲህ ዓይነት መንገድ ይገባሉ የሚል ነው፡፡ እንግዲህ አስተዋይ የሆነ ደቀ መዝሙር ይጠይቅ! ነገሩን ይመርምር እንጂ እንዲሁ ይህን ጥያቄ አይለፍ፡፡ ለመሆኑ መንግሥቱን እየሰበክንና ለሰዎችም እያስተዋወቅን ይሆን? ወይስ በዐውደ ምህረቱ (በጉባኤ) ምን እየተሰበከ ይሆን? እንግዲህ ሁሉም ስብከቱን ይፈትሽ፡፡ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አጅግ አሳሳቢ ጊዜ ላይ ደርሰናልና! እረኛው መንጋውን መጠበቅና ወንጌል ሰባኪውም ለፍጥረት መንግሥቱን ማወጅ ያልቻለበት ወቅት ይመስላል፡፡ የሕዝበ ክርስቲያኑም እርካታ ማጣት ከአንዱ ቤተ እምነት ወደ ሌላዉ ቤተ እምነት የሚያሽከረከረው መንፈሳዊ የሆነ ርሃብና (ጠኔ) ይዞት ይሆን? ታማኝና ልባም መጋቢ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይሰብካል፤





ያስተዋውቃል፤ መንግሥቱንም በሕዝቡ ልብ ያሰፋል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ካልተሰበከ በውጭ ያሉት አይገቡባትም፤ በውስጥም ያሉት አይኖሩባትም፡፡

"ከመጥምቁም ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥት ሰማያት ትገፋለች ግፈኞችም ይናጠቋታል"(ማቴ. 11÷12) ፡፡ ለመሆኑ ይህን ቃል እንዴት ይሆን የምንረዳው? ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመጥምቁ ዮሐንስ ጀምሮ የሰው ልጆችን ልብ ለመግዛትና ለእግዚአብሔር ለማድረግ ሲትመጣ ብዙዎች ገፈተዋታል፡፡ ለምሳሌም መጥምቁ ዮሐንስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመስበኩ ታስሯል፤ በመጨረሻም አንገቱን ቆርጠው ገድለውታል፡፡ እንዲህ እያለ መንግሥቱ እየተገፋች እስከዚህ ደርሳለች፡፡ ምንም እንኳን መንግሥቱ ዋጋ በሚያስከፍል መልኩ ብትሰበክም የሕይወት መስዋዕትነት ቢጠይቅም አሁንም የእግዚአብሔርን መንግሥት በኃይል የሚሰብኩ ሰዎች ይነሳሉ ወይም ይበልጥ ሃይለኛና ለእዉነተኛ ነገር ቁጡ የሆኑ ይነሳሉ በማለት ጌታ ኢየሱስ ይናገራል፡፡ "ግፈኞች" የሚለው ቃል በዚህ ክፍል አመልካችነቱ ጨካኝና ግፍን የተሞሉ የሚል ትርጉም ሳይሆን ይልቁኑ በእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል "violent take it by force" N.k.j.v. ትርጉሙም ኃይለኛና ቁጡ

የሆኑ ሰዎች መነሳታቸውን ያሳያል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይሰበክ ተጻራሪ ሆኖ የሚቀርቡ ቢኖሩ ይህን ገደብ ጥሰው የሚሄዱ ኃይለኛ ትውልድ፣ በጌታና በሃይሉ ችሎት የበረቱና ከመጥምቁ ዮሐንስ ይልቅ መንግሥቱን በታላቅ ድፍረት የሚሰብኩ ቅዱሳን እንደሚነሱ ያመለክታል፡፡

ሰይጣን በዚህ ዓለም ያሉትን ሰዎች ራሱ ባዋቀረው ሥርዓት ይገዛል፡፡ የአገዛዙ መርህ ለእግዚአብሔር መንግሥት ምቹ እንዳይሆኑና መንግሥቱንም እንዲገፉና እንዲቃወሙ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ዔሳው በሄደበት መንገድ እንድሄድ በማድረግ ነው፤ ቃሉም ለትውልዱ እንደማስጠንቀቂያ ተጽፏል፡፡ እንዲህ በማለት "ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንዳሸጠ እንደ ዔሳው፤ ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ" (ዕብ. 12÷16) ይላል፡፡ ለዓለም መመቸት ማለት ለሰይጣን አገዛዝ መመቻቸት ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓለም ያሉትን ሰዎች ከውልደታቸው ቀን ጀምሮ ሰይጣን ለነገሮች የሚሰጡትን ዋጋ ወይም እሴት (Value) ዓለማዊ ይሆን ዘንድ በውስጣቸው አስቀምጣል (Set up) አድርጓል፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔርን መንግሥት በልባቸው ፈፅመው ላለመቀበል ይቃወሚታል ለምን የእግዚአብሔር መንግሥት የዚህ ዓለምን ስርዓት ተጻራ





ስለቆመች፡፡ እስኪ ይህንን ሃሳብ በምሳሌ እንይ "በአንድ ወቅት ሳዳም ሁሴንን ለመጣል የተደረገው ጦርነት በኢራቅ እንደ አበቃ በጦርነት የፈራረሰችውን ኢራቅ መልሶ ለመገንባት ታስቦ የግንባታ ሥራ ጨረታ ወጣ፡፡ ጨረታውንም አብዛኛውን የአሜሪካ ካምፓኒዎች አሸነፉ፡፡ ይህ ሁኔታ ግን ብዙ ኢራቃውያንን አላስደሰተም! ምክንያቱም የምትገነባው ኢራቅ ምን ዓይነት ልትሆን ነው? በሚል ነበር። ኢራቃውያን የሚፈልጉት ኢራቅ ናት? ወይንስ አሜሪካዊያን የሚፈልጓት ኢራቅ? በርግጥ አሜሪካን የገነባቻት ኢራቅ ከአንድ ኢራቃውያን በአገሩ ከሚኖሩ የተሻለ ዕውቀት ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሰይጣንም የዚህ ዓለም ሰዎችን በራሱ ንድፍ (ፕላን) ገንብቷአቸዋልና በቀላሉ በሰዎች ልብ ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋት አይችልም፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት ግን በኃይል ይሰብካል፡፡ ይኸ ኃይል በመጀመሪያ በሰዎች ውስጥ ሰይጣን የገነባውን ግንባታ ያፈርሳል፡፡ በመቀጠልም ሰዎች ለመንግሥቱ መስፋት ይመቹ ዘንድ በውስጣቸው ሥራን ይጀምራል፡፡ ይህም አዲስ ግንባታ ማካሄድን ያመለክታል፡፡ መንግሥቱን በምን አይነት መንገድ ነው የምናስፋው?

## 8.1 ወንጌልን በመስበክ፤

"የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለም::" (1ቆሮ. 4÷20)

ወንጌል የእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ነው:: ለሰዎች ወንጌልን ስንሰብክ የምናስተዋውቀው መንግሥቱን ነው:: የመንግሥቱ ቃል እርሾ በሊጥ ውስጥ ገብቶ ለውጥ እንደሚያመጣ የወንጌሉም ቃል እንዲሁ ወደ ሰዎች ልብ ገብቶ የመቀየር ሥራ ይሰራል:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንግሥቱ ሲናገር ያለው "... የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርስዋ በኃይል ይገቡበታል" (ሉ.ቃ.16÷16) ይላል:: መንግሥቱ ከተሰበከ ሰዎች እየተሻሙና እየተሯሯጡ ወደ መንግሥቱ ይገባሉ ማለት ነው:: ለምን? የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም ላይ ካሉ ብልጭልጭና ብዙዎችን ቶሎ ከሚማርካቸው ነገሮች ሁሉ ስለሚበልጥና ስለሚሻል ነው::

ማንም ሰው የተሻለ ነገር ይመርጣል፣ የተሻለ ሃገር ለመኖር ይፈልጋል:: ብዙ የሃገራችን ሰዎች በተለያየ መንገድ ወደ ተለያየ የዓለም ክፍል በስደትና በሌላም መንገድ ገብተዋል፤ ምክንያታቸውን ብንመረምር የተሻለ ነገር እንዲኖራቸው በመፈልግ ይሆናል:: በአንድ ወቅት ዕድሜው 4 ዓመት የሆነ ልጅ፣ ማሙሽ ስታድግ ምን ለመሆን ትፈልጋለህ ስለው "አሜሪካ መሄድ ነው" በማለት





ነበር :: በጣም ገረመኝ ይኸ ልጅ ገና ትምህርት መጀመሩ ነው:: ደግሞ ኑሮ የሚባለውን ነገር እንኳን እንደሚገባ ማጣጣም አልጀመረም:: ታዲያ እንዴት አሜሪካንን ሊመርጥ ቻለ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ:: እርግጠኛ የሆኑኩት ወላጆቹ ስለ አሜሪካ የሚያወሩትን መልካም ገፅታ ስለ ሰማ እንደሆነ ገመትኩ:: የእግዚአብሔርንም መንግሥት ለሰዎች ሁሉ የተሻለች ሆና ከቀረበችና ከተሰበከች የማይመርጣትና የማይፈልጋት ማንም የለም::

ሰዎች ከዚህ ዓለም ገዢና ከጨለማው መንግሥት ከዳኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ:: የመንግሥቱም ዘር በውስጣቸው ማደግ መስፋትም ይጀምራል::

እግዚአብሔር መንግሥቱን የሚያስተዋውቀው በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አማካኝነት ነው:: ለሰዎችም ወንጌል ሲሰበክ መረጃ ብቻ ሳይሆን የሚሰጣቸው ውስጣቸውን የሚነካውንና የሚለውጥን ኃይልም ጭምር ነው:: ወንጌል በውስጡ የድነት ኃይል ይዛልና (ሮሜ 1÷16)::

## 8.2 መንግሥቱን በቤታችን በማስፋት፤

የመንግሥቱ አገልጋይ ለመሆን በመጀመሪያ በእኛ ውስጥ መንግሥቱ በሃይል መስፋት አለበት፤ ከዚያም

በቤታችን ውስጥ እንዲህ እያለ ወደ ምድራችን ይዘልቃል፡፡

እግዚአብሔር በምድር ላይ የመንግሥቱ ዘር እንዲኖር እንዲሁም በሰው ልቦች ሁሉ እንዲያድግና እንዲቀጥል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቅዱስ ዘር ከምድር እንዳይጠፋ በትውልዱ ላይ ልትሠራ ይገባታል፡፡ እስኪ ለቀጣይ ትውልዱ አስቦ የሰራውን አብርሃምን እንይ እግዚአብሔርም ስለ እርሱ ሲመሰክር እንዲህ ይላል " ጽድቅና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርንም መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና" (ዘፍ.18፥19)፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በምድር ላይ ጽድቅንና ፍርድን የሚያወቅ የመንግሥቱ ዜጋ የሆነ ሰው ይኖር ዘንድ ይወዳል፡፡ ይህም በወንጌል የዳነ ቅዱስ ሕዝብ ነው፡፡ ይህ ቅዱስ ሕዝብ በሥጋ እንኳን የሚወልደው ልጁ የጨለማው መንግሥት አባል እንዳይሆን ጽድቅን፣ ፍርድንና እግዚአብሔርንም ማወቅ ሊያስተምረው ይገባል፡፡ አብርሃም በእርሱ ዘመን ለእግዚአብሔር መሰዊያ ሰርቶ አምልኳል፡፡ ልጆቹ ግን መሰዊያ እንዳያፈርሱ በማሰብ ልጆቹን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲሄዱ ያስተምር ነበር ፡፡

"ልጆች የነገ ነጸብራቅ ናቸው" ይባላል፡፡ ዛሬ እግዚአብሔርን ማወቅ ካላስተማርናቸው፤ ነገ እግዚአብሔርን የማያውቅ





ትውልድ ይነሳል፡፡ ጽድቅ ማድረግን ለልጆች ካላሳየናቸውና ካልተማሩ ነገ ዓመጽ በምድሪቱ ላይ ይነግሳል፡፡ ስለዚህ ከዘራችን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይጠፋ በልጆቻችንና በታዳጊዎች ላይ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ በቅርብ ጊዜ በእንግሊዝ ሃገር በተደረገውን አድማና የሕዝብ ዓመጽ አስመልክተው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲናገሩ የዚህ ሁሉ ችግር ምንጭ ወላጆች ልጆቻቸውን በሞራል ታንጸው እንዲያድጉ አለማደጋቸው እንደሆነ ነገሩን ከመሠረቱ አይተው ሲናገሩ ተስተውለዋል፡፡ ደግሞም በቀጣዩ የሥራ ዘመናቸው ትውልዱን በሞራል (በሥነ ምግባር) አንጸው ለማሳደግ ፊታቸውን ልጆቹ ወደሚገኙበት ቤተ ሰብ ፣ ት/ቤት.... እንደሚያደርጉ ሲናገሩ ተሰምተዋል፡፡

በልጆች ላይ የሚሰጠው አገልግሎት ከቤት እንደሚጀምር ወላጆች ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ አባትና እናት በልጃቸው ላይ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የቤት ስራ መስራት ከቻሉ ቢያንስ የሚቀረውን አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ማግኘት ይችላሉ፡፡ እንጂ ነገር ዓለሙን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ጫንቃ ላይ መጣል ኃላፊነትን በአግባቡ ያለመወጣት ምልክት ነው፡፡ ስለዚህ ወላጆች ልጆቻቸውን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ማስተማር አለባቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ እንደሚባለው ልጆች የምንነግራቸውን ሳይሆን የምናደርጋቸውን ያያሉ

ይሰማሉም፡፡ ስለዚህ ወላጆች ምሳሌነት ያለው ሕይወት በመኖር ልጆች የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደው እንዲከተሉ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

**8.3 መንግሥቱን በሥራችን በማስፋት፤**

ክርስቲያን በተሰማራበት የሥራ መስክ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይሰደብ፣ በጥንቃቄ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ለሥራው የሚያሳየው ባሕርይ ታማኝነትና ትጋት ሊሆን ይገባል፡፡ አላግባብ ትርፍን ለማግኘት ሲል ከዓመጻ ሥራ ጋር በምንም ዓይነት መንገድ መተባበር የለበትም፡፡ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመጽ ይራቅ በሚል መሠረት ላይ መቆም አለበት፡፡

ሌላው ክርስቲያን የመንግሥቱ ዜጋ ስለሆነ በሚያደርገው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት እያሰበ መኖር አለበት፡፡ ገንዘቡን መንግሥቱ ለሚሠፋበት ሥራ እየሰጠ ሰዎች የሚድኑበትና የሚታነጹበትን መንገድ ለማሳደግ መጣር አለበት፡፡ እስኪ ለትምህርታችን እንዲሆን የቃል ኪዳን ሕዝብ የሆኑት እስራኤላዊያን የሚያደርጉትን እንይ፡፡ የእስራኤል ሕዝብ እንደሚባለው የሚገበየው ከወገኑ ጋር እንጂ ከሌላ ህዝብ ላይ አይደለም ይባላል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ ገዢም ሆነ ሻጭ የሚሉት "ጽዮንን" አስብ ብለው ከሚያገኙት ገንዘብ ሁለቱም ወደ ሃገራቸው በመላክ





መንግሥታቸውን የማጠናከርና ግዛታቸውን የማስፋፋት ሥራ ይሠራሉ፡፡ ደግሞም በየትኛውም ዓለም ይኑሩ ተገናኝተው ሊለያዩ ሲል "ለሚቀጥለው ዓመት በኢየሩሳሌም እንገናኝ" በማለት ተስፋ በሰነቀ ሰላምታ "ሻሎም" ብለው ይለያያሉ፡፡

ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር እንዲሰፋ በማሰብ ሊሰራና ይገባዋል እንጂ በምድር ላይ ጥሩ ኑሮ ለመኖር ገንዘብንም ለማካበት ብቻ የሚያስብ ከሆነ የመንግሥቱ ሀሳብ በውስጡ አልገባውምና ለጌታ ታማኝ ባለዓደራ አይደለም፡፡ ገንዘብ መንግሥቱን በማስፋት ሂደት ትልቅ ቦታ አለው፡፡ በተለይ የወንጌል አገልግሎት እንደሚገባ እንዲሄድ ገንዘብ ኅማ ነው ብንል ማጋነን አይሆንብንም፡፡ ስለዚህ ይህንን በመረዳት ወደ ቤቱ ጎተራ ገንዘባችንን በመጨመር፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋት ከእያንዳንዱ የመንግሥቱ ዜጋ ይህ ይጠበቅበታል፡፡ ገንዘባችንን ለመንግሥቱ ሥራ ስንሰጥ የገንዘብን ጌትነት ከላያችን ላይ መሻር እንደሆነ መረዳት አለብን፡፡ ገንዘብን በሚወደው ሰው ውስጥ የጌትነት ቦታ አለው፡፡ ገንዘባችንም ለጌታ የተዋጀ መሆን አለበት፡፡ ይህም ከዓለም ውስጥ በመለየት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ እስራኤላውያን ሲወጡ እነሱ ብቻ

ሳይሆን ገንዘባቸውም (ንብረታቸውም) ጭምር ተዋጅቶአልና፡፡

እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት በመጥምቁ ዮሐንስ መንግስቱ ትመጣለች (ቀርባለች) ተብሎ የተሰበከው (ማቴ. 3÷1-2) ፡፡ ደግሞም በመሲሁ መምጣት በመካከላችሁ ናት የተባለችው (ሉቃ. 17÷20-21)፡፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚሰበከው ይህ የመንግሥት ወንጌል ነው (ማቴ. 24÷14)፡፡ ለጻኑ ቅዱሳን የተሰጠው ታላቅ ተልዕኮ መንግሥቱን ማስፋት ነው፡፡ በዘመን ፍጻሜ ራዕይ ውስጥ ማለትም ዓለምን በክርስቶስ መጠቅለሉ የመንግሥቱ ዜጎች የሚሰተፉበት የእግዚአብሔር የጸና ሃሳቡ ነው፡፡

## ምሥራፉ ዘጠኝ

"በነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ፈቃድ የማይፈርስ ለሌላም ሕዝብ የማይሰጥ መንግሥት ይመሠርታል፤ እነዚያን መንግሥታት ሁሉ ያደቃል፤ እስከ መጨረሻውም ያጠፋቸዋል ይህ መንግሥት ራሱ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።"

(ዳን. 2÷44)

ከሰባቱ መናፍስት እንዲሁም ታማኝ ምስክር ከሙታን በኩርና የምድር ነገስታት ገዥ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ..." (ራእ 1÷4-5)።

ስለ መጨረሻው ዘመን የሚያጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱሳችን ¼ ወይም 25% የሚሆነው ስለመሲሁ መመለስ የሚያወራ እንደሆነ ይናገራሉ። የመሲሁ መመለስ በዋናነት መንግሥቱን በምድር ለመመሥረትና ለሺህ ዓመት የእርሱ ከሆኑት ጋር ለመግዛት እንደሆነ ይታወቃል። አማኞች አሁን በዚህ ዓለም ገዢ በተያዘው ዓለም ቢኖሩም ባለመታከት ግን የሚጠብቁት የመሲሁን መንግሥት በምድር መመስረትና ከእርሱ መንገስን ነው (ራዕ.21÷1-6)።

የክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም መመለስ ግን እውነት ነው? እንዲህ አይነት ጥያቄ በሐዋሪያት ዘመን አንዳንድ ዘባቾች እንደነበሩና በመጨረሻም ዘመን እንደሚነሱ ቃሉ ይናገራል (2ጴጥ. 3÷3-7)። ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ የማይቀርበት ተስፋ ነው። ቃሉም እንደሚል "የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁም ይመጣል አሉአቸው" (የሐሥ.1÷11)። የወንጌል አማኞች የክርስቶስን ዳግም በክብር፣ በአካልና በሚታይ መልኩ





መመለሱን ያምናሉ፤ ምንም እንኳን ከመመለሱ በፊት ባሉት ቅድመ ተከተል ነገሮች ባይስማሙ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ለአማኞች ሁሉ የሚሆን ተስፋ ነው። "ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በእርሳችሁ ተጽናኑ" (1ተሰ. 4÷18) ይላል። የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ለሁሉ ያፅናና ይሆን? ይኼ ጥያቄ በተለይ አማኝ ላልሆኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን አማኝ የሆነውን ብንጠይቅ ምን ይኾን ምላሻችን? በርግጥ ምስጥሩ ለገባው መምጣቱ ያፅናናል፤ እያወቁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለማይኖሩቱ ግን ፍራቻን በውስጣቸሁ ይጭራል።

የክርስቶስ ሁለት መምጣቶች መጽሐፍ ቅዱሳችን ሲያስተምር የመጀመሪያው መምጣት ስለ ሰዎች ልጆች ኃጢአት መስዋት ለመሆን እንደ በግ ለመታረድ ሲሆን (ዮሐ. 1÷29፣ ኢሳ. 53÷1-12)። ሁለተኛ መምጣቱ ግን በአባቱ በዳዊት ዙፋን ለመቀመጥና ለመፍረድ ነው። ይኸም በምድር ላይ ለሺህ ዓመት የሚመራው መንግሥት፣ በንጉስ በኢየሱስ በመሆኑ ፍፁም ሰላማዊና ደስታ የሞላበት (ኢሳ. 2÷4፣ 11፤ 1-9) ይሆናል።

የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት መገለጥ እንደ ሰንሰለት ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የተያያዘ ትምህርት ነው። በብሉይ ኪዳን ለዳዊት በዙፋን የሚቀመጥ እንደሚነሳ

የሚጠራው፡፡ በዳዊት ዘመን የጣኦት አምላኪና የጣኦታት መስገጃ አልነበረም፡፡ ዳዊት ሕዝቡን ይዞ እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር፡፡ የዳዊት ድንኳን አምልኮ የማይቋረጥበት ሌሊትና ቀን የሚዘምሩና የሚያመልኩ ሰዎች ያሉበት ድንኳን በመሆኑ በአሞጽ ትንቢት የወደቀውን የዳዊትን ድንኳን አድሳለው በማለት በሺሁ ዓመት መንግሥት የሚኖረውን አምልኮ በዳዊት ዘመን በነበረው ልክ እንደሚያደርሰው ቃሉ ይናገራል፡፡ ዳዊት ለእግዚአብሔር ለመዘመር ሁሉንም ዓይነት መሣሪያ የተጠቀመ ሰው ነበር (መዝ 150÷3-6)፡፡ በዚያን ዘመን የዜማ ዕቃዎችን እየተጫወቱ የሚያመሰግኑ ሰዎች እንኳን እስከ አራት ሺህ የሚደርሱ እንደነበሩ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (1ዜና. 23÷5)፡፡

በዚህም በክህነት መንግሥት ውስጥ ዓይነተኛ የሆነው የዜጎቹ ሥራ አምልኮ ነው (ዘካ. 14÷16-19)፡፡ የካህን ዋነኛው ሥራ ደግሞ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ማቅረብ ሲሆን በመሲሁ መንግስት ውስጥ ሁሉም ዜጋ ካህን በመሆኑ የማይቋረጥ የአምልኮ መሰዋዕትን ያቀርባሉ፡፡





## 9.3 የሰላም ዘመን ይሆናል፤

"... ሰይፋቸውንም ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሳም ሰልፍም ከእንግዲህ አይማሩም (ኢሳ. 2÷4)፡፡

በብሉይ ኪዳን የሰላም ዘመን ተብሎ የሚጠቀሰው የዳዊት ልጅ የሰለሞን ዘመን ነው:: ይሄ ዘመን ለእስራኤል ወርቃማ ዘመኖች (Golden Ages) በመባል ይታወቃል፡፡ እግዚአብሔር አስቀደሞ የንጉስ ሰለሞን ዘመን፣ የሰላም ዘመን እንደሚሆን ለአባቱ ለዳዊት ተናግሯል "...እነሆ የዕረፍት ሰው የሚሆን ልጅ ይወለድልሃል፤ በዙሪያው ካሉ ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ፤ ስሙ ሰሎሞን ይባላልና በዘመኑም ሰላምንና ጸጥታን ለእስራኤል እሰጣለሁ " (1ዜና.22÷9-10) በማለት፡፡

በንጉስ ሰለሞን ዘመን ምን ሆነ? የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ታነፀ፣ የእግዚአብሔር ታቦት ከድንኳን ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ፣ እስራኤል በዙሪያዋ ካሉት ጠላቶች አረፈች ፣ ታይቶ የማይታወቅ ምናልባትም እንደ ሃገር በሰው ልጅ የአስተዳደር ዘመን ያልታየ ብልፅግና ውስጥ የገቡበት ዘመን ነው፡፡

መሲሁ የሚመራው መንግሥት ከዚህ የላቀ ብልፅግናና ስኬት ያለበት ነው፡፡ ጦርና የጦር ወሬ በዚህ በሺሁ ዓመት መንግሥት ጊዜ አይሰማም (ኢዩ. 3÷17-21)፡፡ ለምን የክፉ

የእግዚአብሔር መንግሥት አስተዳደር በተለየ መልኩ ይታያል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ጥበብ ባለው መልኩ ሲገልፅ "መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" (ማቴ. 6÷10) ብሏል፡፡

የእግዚአብሔር ቅድስናና ክብር በሰማያዊው ዙፋኑ ላይ ሆኖ እግዚአብሔርን ለማክበር የማይበቃ አገልግሎት የሚያገለግሉትን ፍጥረታት ሁሉ ይገዛል፡፡ ምንም እንኳን ፍጥረታት በምድር ላይ ቢያምፁና የእግዚዘብሔርን ንጉስነት ላለመቀበል ቢገፏት የእግዚአብሔርን መንግሥት በመቃወም የከፋት መንግሥታት ቢነሱም በመገለጡ ቀን ሁሉም እንደሚሻርና ሰማያዊው ዙፋን ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር ቃሉ ይናገራል (መዝ. 97÷1-2)፡፡

እግዚአብሔር በኃጢያት ምክንያት የሚሞተውን ሰውነት በመለወጥ የማይሞትና የማይበሰብስን አካልን ያለብሰዋል፡፡ ሁሉም በሚታደስበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቸዋን ትገዛላች፡፡ በተጨማሪም በሰማያዊ መንግሥት እንደሚሆነው በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መገዛት በምድር ላይ ይሆናል (1ዜና 16÷31፣ መዝ. 91÷1-2)፡፡ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው በመሲሁ በምድር ላይ መመለስ ጊዜ ነው፡፡





አብርሃምና ልጆቹን ለእግዚአብሔር የተለዩ ሕዝቦች አድርጎ መምረጡ ለእግዚአብሔር መንግሥት በዋናነት በእስራኤል ሕዝብና መሬት ላይ ተወስኖ እንደ ነበር መረዳት ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር ንጉስነቱን እስራኤልን ከግብፅ አገዛዝ ባወጣበት እና ወደ ቃል ኪዳን መሬት በመጣበት ጊዜ አረጋግጧል (ዘፀ. 15)፡፡ በዳዊትና በሰለሞን እንዲሁም በዳዊት ልጆች እስራኤል በግልፅ የምትታወቅ ግዛት እድትሆንና የእግዚአብሔር አገዛዝ መገለጫ እንድትሆን ፈልጓል (1ዜና. 19÷13፣ 2ዜና. 5-6፣ 1ዜና. 28÷2)፡፡ ይህ በጎሳና በመልካ ምድር የተወሰነ ግዛት በራሱ የመጨረሻ አልነበረም፡፡ በተቃራኒ የብሉይ ኪዳን እስራኤል የእግዚአብሔር መንግሥት መግለጫ ነበረች (ዘፍ.17÷17-18፣ 18÷1-8፣ ሮሜ 4÷13-17)/፡፡ የእስራኤልና የይሁዳ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ በእስራኤል ዘንድ ያለው የእግዚአብሔርን መንግሥት በቀውስ ውስጥ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከስደት በኃላ ኀጢአትን ከምድር ላይ እንዲያስወግዱና ያለምንም ተቃውሞ መንግሥቱን እንዲመስርቱ ይናገራል (ሚክ. 4÷1-13)፡፡ በዚህም ጊዜ እስከ ምድር መጨረሻ በይሁዳና በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይሆናል (1ዜና. 16÷13-36፣ ኢሳ. 52÷7-15፣ መዝ. 67÷67)፡፡

## በጸሓፊው በሕትመት የበቁ መጻሕፍት

- ክርስቶስን ወደመምሰል ማደግ (2003)
- የእግዚአብሔር መንግስት (2004)

## ወደ ፊት ለህትመት የተዘጋጁ

- የእግዚአብሔር ስቅድ
- ሕያው ስምሰኮ
- መንፈሳዊነት